# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 171 የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00


ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## የኢትዮጵያና የኬንያ መሪዎች ውይይት

## የሀገሮቹን የወደፊት ቁልፍ የትብብር መስኮች የለየ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ኬንያ ያደረጉት ውይይት የቆየውን ትስስራቸውን ያጠናከረ ብቻ ሳይሆን የወደፊት ቁልፍ የትብብር መስኮችንም የለየ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኬንያ ባደረጉት ይፋዊ የሁለት ቀናት ጉብኝት በፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ በስቴት ሀውስ ኬንያ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

የአቀባበል ሥነሥርዓቱ ሁለቱ መሪዎች እና የልዑካን ቡድኖቻቸው በሁለትዮሽ፣ ቀጣናዊ እና ባለብዙ ወገን ጉዳዮች ላይ እያደረጓቸው ያሉ ጉልህ ግንኙነቶች እና ውይይቶች ጅማሮ መሆኑ ተገልጿል።

የኢትዮጵያና የኬንያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከ40 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ጤና መድህን አባልነታቸውን አድሰዋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎት ከ40 ሚሊዮን በላይ ዜጎች አባልነታቸውን ማደሳቸውን የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

በአገልግሎቱ የአባላት አስተዳደርና ሀብት አሰባሰብ ዳይሬክተር አቶ ጉደታ አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በባለፈው ዓመት በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ ከሆኑት 55 ሚሊዮን በላይ አባላት መካከል በዘንድሮው በጀት ዓመት ከ40 ሚሊዮን በላይ ዜጎች አባልነታቸውን

ከ40 ሚሊዮን በላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ሀዱሽ አብርሀ

ሰላማዊት ካሳ

## 128ኛው የዓድዋ በዓል

### ለሀገር መስዋዕት መሆን ያለውን ትርጉም በሚያሳይ መልኩ ይከበራል

- ‘የሁለት ውሃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ’ በሚል የታተመ የፖሊሲ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል

ገጽ 4

## 128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ክብሩን በሚመጥን መልኩ ይከበራል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- 128ኛው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ክብረ በዓል በታላቅ ድምቀት የድሉን ክብር በሚመጥን መልኩ ተከብሮ እንደሚውል የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል አበባው ታደሰ ገለፁ። በዓሉን ለማክበርም ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መጠናቀቃቸውን የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴዎችም ተናግረዋል።

የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴዎችን ሪፖርት ያዳመጡት የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል አበባው ታደሰ፤ 128ኛው የዓድዋ ድል ፒያሳ በሚገኘው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ላይ ይከበራል ብለዋል።

ወቅቱን በሚዘክር እና ክብሩን በሚመጥን መልኩ የዓድዋ ድል መታሰቢያ እንደሚከበር የገለፁት ጀኔራል አበባው፤ በዓሉን ለማክበር በወጣው ዕቅድ መሠረት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸውም ተናግረዋል።

128ኛው የዓድዋ ድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ሰማኸኝ ጋሻው

# ዓድዋ የድሉን ግዝፈት ያህል አልተጠናም

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በታሪካዊ የጥናት ዘርፍ ዓድዋ የድሉን ግዝፈት ያህል ተጠንቷል ብለው እንደማያስቡ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር እና ተመራማሪ ገለጹ፡፡

የታሪክ ተመራማሪው ሰማኸኝ ጋሻው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ ዓድዋ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ የታሪክ እጥፋቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የሰው ልጅን የእርስ በእርስ ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበትም መልክ ካስያዙ ክስተቶች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ ይሁንና የድሉን ግዝፈት ያህል በታሪካዊ የጥናት ዘርፍ ተጠንቷል ብሎ ለመናገር ከባድ ነው፡፡

ዓድዋ ለሰው ልጆች በተለይም ደግሞ ለአፍሪካውያን ያስገኘውን ጠቀሜታ ያህል ተዘክሯል ብዬ አላምንም ያሉት መምህር ሰማኸኝ፣ እንዲሁም ለድሉ ግንባር ቀደም ባለቤት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ራሷ የሚጠበቅባትን ያህል ትኩረት አልሰጠችም ነበር ብለዋል።

«ዛሬ ላይ የዓድዋን 128ኛ ዓመት እያከበርን ብንሆንም ይህን ሁሉ ዓመታት ዓድዋ በስሙ የሚጠራ አንድም ብሔራዊ ተቋም አልነበረውም፡፡ ታሪክ የተሠራባቸው የዓድዋ ተራሮች ዛሬም ምንም ዓይነት መሠረተ ልማት የላቸውም፤ ለጥናትና ምርምር፣ ለቱሪስት መስህብ ሊውሉ የሚችሉ ተቋማት ዛሬም አይስተዋሉም» ሲሉ ተናግረው፤ ድሉ ታላቅ እና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ከሚሰጣቸው ድሎች መካከል አንዱ እንደመሆኑ በአግባቡ ሊጠና የሚገባው ነው ብለዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፤ አፍሪካውያን ድሉ የጋራቸው መሆኑን ተገንዝበው ታሪኩን የሚመጥን ሥራ ሲሠሩ አይስተዋሉም። ዛሬም ድረስ ለዓድዋ መታሰቢያ ሊሆኑ የሚችሉ የጥናት ማዕከሎች በአፍሪካ ሀገሮች አይስተዋሉም። ይህ የራስን ታሪክ ከማቃለል፤ የተከፈለውን መስዋዕትነት ካለመረዳት እንዲሁም ታሪካዊ ፋይዳውን በአግባቡ ካለማወቅ የሚመነጭ ይመስላል።

የታሪክ ተመራማሪው ሰማኸኝ፣ በእርግጥ ከቅኝ ግዛት ዘመን በኋላ በአፍሪካ የተመሠረቱ በርካታ መንግሥታት ከአዲሱ ቅኝ ግዛት አስተሳሰብ (Neocolonialism sentiments) ነፃ የወጡ ናቸው ብዬ አላምንም። አሁንም ድረስ በድሮ ቅኝ ገዥዎቻቸው ተጽዕኖ ስር በመሆናቸው ለዓድዋ የሚሰጡት ትኩረት እጅግ ያነሰ እንዲሆን አድርጎታል ሲሉም አስረድተዋል።

በታሪካዊ የጥናት ዘርፉም ቢሆን ዓድዋ የታላቅነቱን ያህል ተጠንቷል ብዬ አላስብም የሚሉት የታሪክ ተመራማሪው፣ ለምሳሌ በዓድዋ ጦርነት ላይ ሥነሕይወታዊ ጦርነት (Biological war) በኢትዮጵያ ላይ ተፈፅሟል ብዬ አስባለሁ ብለዋል።

በወቅቱ ፋሽስት ኢጣሊያ «አባ ሰንጋ» በተባለ የከብት በሽታ የተጠቃ ከብት በምፅዋ ወደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ከፍተኛ ጉዳት አድርሳለች ያሉት ምሁሩ፤ በዚህ የተነሳ በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ በታሪክ «ክፉ ቀን» የተባለው ዘመን እ.ኤ.አ ከ1889 እስከ 1892 ተከስቶ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

ይህ ክስተት ኢትዮጵያውያንን ክፉኛ ከመጉዳቱም በላይ ኢጣሊያ ሀገራችንን ለመውረር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር አስባ የፈፀመችው እኩይ ሴራ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ነገር ግን እስካሁን በጥናት ተደግፎ ሊቀርብ አልቻለም ብለዋል።

# በዞኑ በኢንቨስትመንት ዘርፍ መዋለ ንዋይ ለማፍሰስ ለሚሹ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል

**ዳግማዊት አበበ**

ወላይታ ሰዶ፡- በዞን በኢንቨስትመንት ዘርፍ መዋለ ንዋይ ለማፍሰስ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን የወላይታ ዞን አስታወቀ፡፡

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ወላይታ ዞን ሰባት በር መወጫና መግቢያ ያለው ሲሆን ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ያለበትም ነው፡፡

ዞኑ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ያለበት መሆኑ በተለይ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ እየተጠቀመባቸው ካሉ ዘርፎች አንዱ ቱሪዝም ነው ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ በወላይታ ዞንም የቱሪዝም መዳረሻ የሆኑ እንደ ዳሞታ ተራራ፣ አጆራ ፏፏቴ፣ ጊቤ ሰው ሠራሽ ሐይቅና የተለያዩ ዋሻዎችን ጨምሮ ብዙ የቱሪስት መስህቦች የሚገኙበት አካባቢ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም አካባቢው በመሠረተ ልማት የተሻለ በመሆኑ ለውጭም ሆነ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ መኖሩን ጠቁመው፤ በዞኑ ባሉ ሰባት መውጫና መግቢያ በሮች በስድስቱ



አቶ ሳሙኤል ፎላ

ደረጃቸውን የጠበቁ የአስፋልት መንገድ እንዲሁም አንዱ መንገድ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በጠጠር ተገነባ ነው ብለዋል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን በተመለከተ ለአካባቢው ተብሎ 45 ሜጋ ዋት የቀረበ ሲሆን በዚህም የትኛውም ባለሀብት በዞኑ በየትኛውም ዘርፍ መዋለ ንዋዩን ቢያፈስ በኃይል አቀርቦት ረገድ ምንም ዓይነት ስጋት አይኖርም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሌላው በዞኑ በርካታ ቁጥር ያላቸው የተማረ የሰው ኃይል ያለበት ነው ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ ይህም በግሉ ዘርፍ ወደ ዞኑ መጥቶ ኢንቨስት ለማድረግ የተማረ ሰው እጥረት እንደሚያጋጥመው ተናግረዋል፡፡

አቶ ሳሙኤል፤ በዋናነት አንድ ባለሀብት ወደ አንድ አካባቢ ሄዶ ኢንቨስት ለማድረግ የሰላም ሁኔታው ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸው፣ በዚህም ወላይታ ዞን ምንም ዓይነት ኮሽታ የሌለበትና አስተማማኝ ሰላም ያለበት ነው፡፡ በዚህም በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ባለሀብቶች ወደ ዞኑ በመምጣት ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎችን እንዲሁም ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመገንባት ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

የዞኑና የከተማ አስተዳደርም በዞኑ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት ላላቸው የግል ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦት በበቂ ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ ሰፊ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ ባለሀብቶችም ያለውን ዕድል በመጠቀም ወደ ዞኑ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# "አንቷን ጋሊንዶ በቁጥጥር ስር የዋለው በግለሰብ ደረጃ በፈጸማቸውና በተጠረጠረባቸው ወንጀሎች ነው"

## - የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ለ37 ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ዘገባ ሽፋን ለመስጠት የመገናኛ ብዙኃን ፍቃድ አግኝቶ ወደ ኢትዮጵያ የገባው አንቷን ጋሊንዶ በቁጥጥር ስር የዋለው ከተሰጠው ፍቃድ ውጪ በጋዜጠኝነት ሙያ ሽፋን ሲንቀሳቀስ በመገኘቱ መሆኑን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

የአገልግሎቱ ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ እንደገለጹት፤ ፈረንሳዊ ዜግነት ያለው አንቷን ጋሊንዶ በቁጥጥር ስር መዋሉን ተከትሎ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን የተሳሳቱ ዘገባዎችና መረጃዎች እየወጡ ይገኛሉ፡፡

ጉዳዩን ከግለሰቡ የሥራ ሁኔታ፣ ዜግነት እና ከሌሎች ጉዳዮች ጋር የማያያዝ ሁኔታዎችን መመልከት ችለናል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ እየተናፈሰ የሚገኘው መረጃም የተሳሳተ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ለአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ የሚገባ ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ ከመጣበት ዓላማ ውጪ መሥራት ሕገ ወጥ መሆኑ የሚታወቅ፣ የትኛውም ዓለም ያለ፣ በተለይም ትላልቅ የዲፕሎማሲ ሁነቶችን የሚያዘጋጁ ሀገራት በግልጽ የሚያስቀምጡት ሕግ ነው ብለዋል፡፡

በቁጥጥር ስር የዋለው ለብሔራዊ ደህንነት ስጋት በሚሆኑ ጉዳዮች ተሰማርቶ በመገኘት ወንጀል ተጠርጥሮና ጉዳዩም በፍርድ ቤት እየታየ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ግለሰቡ በቁጥጥር ስር የዋለው ወደ ሀገር ውስጥ ከገባበት ዋነኛ ዓላማ ውጪ በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳዮች ትኩረት በማድረግ መረጃ ለመሰብሰብ ባደረገው ጥረት፣ ጥቆማዎችን እና መረጃዎችን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

የካቲት 14 ቀን 2016 ዓ.ም በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሎ ጉዳዩ እየተጣራ ይገኛል፣ በ48 ሰዓታት ውስጥም ፍርድ ቤት ቀርቧል፣ ፖሊስ በግለሰቡ ላይ እያደረገ ያለውን ምርመራ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ተፈቅዶለት የማጣራት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝም አመልክተዋል፡፡

ከ500 በላይ የሚሆኑ የውጭ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ለ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ



ሰላማዊት ካሳ

ዘገባ ሽፋን ለመስጠት ወደኢትዮጵያ መግባታቸውን አስታውሰዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንቷን ጋሊንዶ የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ዘገባ ሽፋን እሰጣለሁ በሚል መሆኑንም አንስተዋል፡፡

የካቲት 05 ቀን 2016 ዓ.ም ሀገር ውስጥ መግባቱን የጉዞ መረጃው እንደሚያሳይ፤ ሆኖም ያገኘውን ፍቃድ በመጠቀም በጋዜጠኝነት ሙያ ሽፋን ተቃራኒ የሆኑ ተግባራትን ሲፈጽም መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

የዘገባ ፍቃድ አግኝቶ ወደ አዲስ አበባ ከገባበት ቀን ጀምሮ ከመጣበት ዓላማ ፍጹም ተቃራኒ የሆኑና ከመጣበት ዓላማ ውጪ የሆኑ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን የሚያሳዩ መረጃዎች መገኘታቸውን አመልክተዋል፡፡

በተለይም የኢትዮጵያን የውስጥ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሲሞክር ነበር፣ በዚህም ደግሞ የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎችንና አመራሮችን ሲያነጋግር እንደነበር ጠቁመዋል፡፡

የማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎችን እና የሀገር ውስጥ የፖለቲካ ጉዳዮች ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ ከሚያስባቸው አካላት ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ሲያሰባስብ መቆየቱንም ለመገንዘብ ተችሏል ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል፡፡

# «ዓድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ-መንግሥት ግንባታ»

## በሚል ሲካሄድ የቆየው ንቅናቄ ነገ ይጠናቀቃል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- «ዓድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ» በሚል መሪ ሃሳብ ከጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው የሰላም ንቅናቄ ነገ እንደሚጠናቀቅ የሰላም ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሰላም ሚኒስቴር ንቅናቄው አሁን ያለበትን ደረጃ ለማሳወቅ በትናንትናው ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሁለት ሰፋፊ የንቅናቄ መድረኮችን ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡ የመጀመሪያው በኢትዮጵያ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ የተካሄደ ሲሆን ሁለተኛው ወጣቱ የማኅበረሰብ ክፍል ላይ ያተኮረ ነው ብለዋል፡፡



ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር)

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሃሳብ መፍለቂያና ከፍተኛ ምሁራን የሚገኙባቸው ማዕከላት ናቸው ያሉት ዶክተር ከይረዲን፤ በዚህም «ዓድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ» በሚል መሪ ሃሳብ በሦስት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ውይይት ተካሂዷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው ጉዳዮቹ የኢትዮጵያ የጋራ ማንነት፣ የጋራ እሴት እና ብሔራዊ ጥቅም ምንድንናቸው የሚሉ መሆናቸውን አንስተው፤ በእነዚህ ጉዳዮች ላይም ምሁራን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲሁም ማኅበረሰቡ በስፋት ሲወያዩበት መቆየቱን ጠቁመዋል፡፡

ንቅናቄው እስካሁን በ45 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካሄዱን ገልጸው፤ በቀጥታ ከ20ሺህ በላይ ምሁራንና የዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ ተሳታፊ መሆናቸውን አንስተዋል።

በተጨማሪም ከ40 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በተለያዩ መረጃ መስጫ አማራጮች ንቅናቄው ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል ሲሉ ገልፀዋል።

ሀገራችን ከፍተኛ የወጣት ቁጥር አላት ያሉት ዶክተር ከይረዲን፤ በሁለተኛው ንቅናቄም እነዚህ ወጣቶች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ በንቃት እንዲወያዩ ከማድረግ አኳያ ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር በመሆን ላለፈው አንድ ወር በእነዚህ ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

በዚህም በቀጥታ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ወጣቶች በንቅናቄው መሳተፋቸውን ገልጸው፤ ይህን የንቅናቄ መድረክም በተለያዩ አማራጮች ለ10 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተደራሽ መሆኑን ተጠቁመዋል።

በአጠቃላይ በሁለቱ የንቅናቄ መድረኮች ከ50 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሲወያይ መቆየታቸውን አስታውቀዋል፡፡

በእነዚህ ዓይነት ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በዚህ መጠን ሰፊውን ማኅበረሰብ የምናወያይ ከሆነ ጠንካራ ማንነት፣ ጠንካራ እሴት፣ ጠንካራ ብሔራዊ ጥቅም ያለን ሕዝቦች መሆናችንን ማረጋገጥ እንችላለን ያሉት ዶክተር ከይረዲን፤ ይህ ከጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የቆየ የሰላም ንቅናቄ የካቲት 22 በዓድዋ ዋዜማ እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል፡፡

በመዝጊያ መርሐግብሩም ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች፣ ምሁራኖች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እንዲሁም የወጣት ተወካዮች ይገኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

# የፒኮ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ከሦስት ሺህ በላይ ነዋሪዎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያደርጋል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በሚያዝያ ወር የሚጠናቀቀው የፒኮ የውሃ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ከሦስት ሺህ በላይ ነዋሪዎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንደሚያደርግ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የታዳሽ ኃይል ምርምር ማዕከል አስታወቀ፡፡

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ክርስቲያን ኤይድ ከተሰኘ ግብረ ሠናይ ድርጅት ጋር በመተባበር በ18 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር ወጪ በካምባ ወረዳ ማይጻሌ ወንዝ ላይ አነስተኛ የውሃ ኃይል ማመንጫ እያስገነባ ይገኛል፡፡

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲው የታዳሽ ኃይል ምርምር ማዕከል ተመራማሪና የፒኮ ኃይድሮ ፓወር የፕሮጀክቱ ዋና አስተባባሪ አቶ በየነ ፈዬ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ትናንሽ ወንዞች ላይ አዲስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለገጠር ማኅበረሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል ክፍተትን ለመሙላት እየሠራ ነው፡፡ ክርስቲያን ኤይድ ከተሰኘ ግብረ ሠናይ ድርጅት ባገኘው የስምንት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ድጋፍ አማካኝነት ሥራው መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ፒኮ ሀይድሮፓወር ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ 15 ኪሎዋት ኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ይኖረዋል፡፡ 600 አባወራዎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ በአማካኝ ከ3 ሺህ በላይ የአካባቢው ነዋሪዎችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ወደፊት የነዋሪዎች ቁጥር ሲጨምር እጥረት እንዳይፈጠር የኤሌክትሪክ ኃይሉን በእጥፍ ለማሳደግ በሚያስችል ፕሮጀክት መነደፉን ጠቁመው፤ ፕሮጀክቱ በአሁኑ ጊዜ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን 160 ሜትር ቦይ ዝርጋታና 90 በመቶ የሲቪል ስትራክቸር ሥራ ተጠናቋል ብለዋል፡፡

ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ወደ ቦታው እየተጓጓዙ መሆኑን ጠቁመው፤ ዘንድሮ ሚያዝያ ወር ላይ ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ አቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የፒኮ ሀይድሮፓወር ፕሮጀክት በአንድ ዓመት ለማጠናቀቅ በማቀድ መሠረቱ በ2014 ዓ.ም መጣሉን የገለጹት አቶ በየነ፤ ወደ ፕሮጀክቱ የሚወስድ የመንገድ



አቶ በየነ ፈዬ

መሠረተ ልማት አለመኖር፣ ለፕሮጀክቱ መጓተት፣ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የተሽከርካሪዎች ፍላጎት አለመኖርና የሲሚንቶ እጥረት ዋና ዋናዎቹ ችግሮች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ለፕሮጀክቱ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲው በዓይነትና በገንዘብ ብዙ እገዛ እያደረገ ነው ያሉት ተመራማሪው፤ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የኤሌክትሪክ ገመድ ዝርጋታ በዩኒቨርሲቲው ተሸፍኗል። ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ በጥሬ ገንዘብ ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ በየነ ገለጻ፤ ፒኮ ሀይድሮ ፓወር ወደ ሥራ የተገባው አስፈላጊ መስፈርቶች አልፎ ነው፡፡ ዲንጋሞ ከአርባ ምንጭ 150 ኪሎ ሜትርና ከዋና ኤሌክትሪክ መስመር በ50 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ በአካባቢውም ሦስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሁለት የጤና ማዕከል፣ አምስት የሃይማኖት ተቋማት፣ አንድ ቴክኒክና ሙያ ተቋምና አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መኖሩን ገልጸዋል፡፡

የፒኮ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የደን መጨፍጨፍንና በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚኖረው የሥራ ጫና በመቀነስ ረገድ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸው፤ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ መሆኑና ማኅበረሰብን አለማፈናቀሉ ሌላው የፕሮጀክቱ ጥቅም መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲን ተሞክሮን ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋት የገጠሩን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ተመራማሪው አብራርተዋል፡፡

# በክፍለ ከተማው የትራፊክ ደንብን የሚጥሱ እግረኞች ቅጣት ተጀመረ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የትራፊክ ሕግና መመሪያን የጣሱ እግረኞች የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ እንደሚያደርግ በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ምስጋና ፋንታ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በለሚ ኩራ ክፍለከተማ ከተሽከርካሪ በተጓዳኝ እግረኞችን መቅጣት ሥራ በጎሮ አደባባይ ተጀምሯል። በዚህም የትራፊክ ሕጎችን እና መመሪያዎችን የጣሱ እግረኞች የማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

ጽሕፈት ቤቱ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የሚገኙ የትራፊክ ፖሊሶች የትራፊክ ሕግና መመሪያ የጣሱ እግረኞችን የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ ደንብ አዘጋጅቷል ያሉት አቶ ምስጋና፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል። ይህም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል ብለዋል።

የቅጣቱ ክብደት እንደ ጥሰቱ ዓይነት እና በሕዝብ ደህንነት በሚኖረው ተጽእኖ የሚወሰን ሲሆን ይህም ከ40 እስከ 80 ብር የሚደርስ ነው ያሉት አቶ ምስጋና፤ ይህ አዲስ አካሄድ እግረኞች በኃላፊነት እንዲጓዙ እና በቸልተኝነት የሚደርሱ አደጋዎችን ለመቀነስ ያለመ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ምስጋና ገለፃ፤ ይህ ዓላማ የትራፊክ ሕግና ደንቦችን በሚጥሱ እግረኞች ላይ ቅጣት የሚያስከትል እንደሆነ ተናግረዋል። የትራፊክ ፖሊሶች እግረኞች የትራፊክ ሕግን እንዲያከብሩ በተጨናነቁ መገናኛዎች እና የእግረኛ ማቋረጫ ቦታዎች ላይ ተሰማርተው በመከታተል ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል።

እነዚህ እርምጃዎች የትራፊክ ሕጎችን የመከተል አስፈላጊነት፣ ሕግን ባለማክበር ስለሚኖሩ አደጋዎች እና ኃላፊነት የሚሰማው ባህሪ በመንገድ ደህንነት ላይ ስላለው አወንታዊ ተፅእኖ እግረኞችን ለማሳወቅ ይረዳል ያሉት አቶ ምስጋና፤ እግረኞች የትራፊክ ደንቦችን እንዲያከብሩ ያበረታታል ብለዋል።



አቶ ምስጋና ፋንታ

ከአስፈፃሚው ተግባራት ጋር በመተባበር ኃላፊነት የሚሰማው የእግረኛ ባህሪን ለማሳደግ የትምህርት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተጀምረዋል ያሉት አቶ ምስጋና፤ እነዚህን መልዕክቶች በብቃት ለማሰራጨት በትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖት ተቋማት እና በማኅበራዊ ሚዲያ እየተሰራጨ እንደሆነ ተናግረዋል።

«የትራፊክ ሕግና ደንቦችን ለራስ ደህንነት ሲባል ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው። እነዚህም ከአካላዊ ጉዳትና ከሞት ይጠብቃሉ» ያሉት አቶ ምስጋና፤ የእግረኛው ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ሥራውን አዳጋች እንደሚያደርገውም ጠቁመዋል፡፡ ነገር ግን የሰውን ሕይወት ከአደጋ ለመከላከል አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ተገቢ ነው ብለዋል።

# 128ኛው የዓድዋ በዓል ለሀገር መስዋዕት መሆን ያለውን ትርጉም በሚያሳይ መልኩ ይከበራል

## - 'የሁለት ውሃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ' በሚል የታተመ የፖሊሲ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- 128ኛው የዓድዋ ድል ክብረ በዓል የሀገር ፍቅርንና ለሀገር መስዋዕት መሆን ያለውን ትርጉም በሚያሳየው መልኩ በተገነባው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ውስጥ እንደሚከበር የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

ኢትዮጵያ በዓባይና በቀይ ባሕር ላይ ያላትን አቋም የሚያንጸባርቀው የፖሊሲ ሰነድ ዛሬ ይመረቃል፡፡

የአገልግሎቱ ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ 128ኛው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ክብረ በዓል የኢትዮጵያውያን የጋራ ድል እና ለአፍሪካም ተምሳሌት እንደመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ክብሩን በሚመጥን መልኩ ይከበራል፡፡

አከባበሩ መከላከያ ሰራዊት ከጀግኖች አባቶች የወረሰውን ጽኑ እሴት በማስቀጠል የአሁኑን ሰራዊት አኩሪ ድሎችና መልካም ገጽታ በሚያጎላ መልኩ ይሆናል። ጀግኖች አርበኞች የሠሩትን አኩሪ ድል ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስረክቡበት ይሆናል፡፡

በዓሉ በሁሉም ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ በተቋማትና በመላው ዓለም በሚገኙ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች የሚከበር መሆኑን አክለዋል፡፡

በዓሉን በማስመልከት የሚካሄዱ ሁነቶችን በበላይነት የመከላከያ ሚኒስቴር የሚያስተባብረው ሲሆን፤ በጠቅላይ መምሪያ ደረጃ በዋና መምሪያዎች፣ በተለያዩ ኃይሎች፣ በኮሮች፣ በእዞች፣ በክፍለ ጦሮችና ተመጣጣኝ እስታፎችን ማዕከል አድርጎ የሰራዊቱን ጀግንነትና መስዋዕትነት በሚያጎላ መልኩ ይታሰባል ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት የቆዩ ችግሮችና ቀጣይ ዕጣ ፈንታ የተወሰነው በዓባይ ወንዝና በቀይ ባህር ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የውሃ አካላት የኢትዮጵያን ጂኦ ፖለቲካ፣ ብሔራዊ ደህንነትን በመወሰን ትልቅ ሚና ያላቸው ሀብቶች ናቸው፡፡

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የተዘጋጀውና ኢትዮጵያ በዓባይና በቀይ ባሕር ላይ ያላትን አቋም የሚያንጸባርቅ የፖሊሲ ሰነድ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል፡፡ ሰነዱ ዘላቂና ለሀገር ህልውና ተግዳሮት የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

የፖሊሲ ሰነዱ የዓባይ ተፋሰስና የባሕር በር ጉዳይን በዝርዝር ይቃኛል፤ በዓባይ ተፋሰስ የውሃ ተጠቃሚነት ላይ ኢትዮጵያ ጉልህ ሚና መጫወት ይገባታል በሚል በስፋት የሚዳስሰው ክፍል ተካትቶበታል፣ የሕግና የፖሊሲ ሰነድ የተካተተበት መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የባሕር በርን ለማግኘት የተደረገውን የትግል ጉዞ ከታሪክ አንጻር በስፋት የዳሰሰ መሆኑንና ስድስት ምዕራፎች ማካተቱን ጠቁመዋል፡፡

የተጋረጠውን ችግር ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ግልጽ ስትራቴጂ የያዘ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምን ለማረጋገጥ የሚያግዝ መሆኑንም ተናግረዋል።

በሌላ በኩልም ሰሞኑን አሳዛኝ የትራፊክ አደጋዎች ክስተት እየተሰማ ነው ያሉት ሰላማዊት፤ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የሚገኘውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በመንግሥት የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ቢሆንም አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንዳልተቻለ አንስተዋል፡፡

በስድስት ወራቱም በተከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች አንድ ሺህ 358 ዜጎች ሕይወት መቀጠፉን ጠቅሰው፤ ያም ሆኖ ግን ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ514 መቀነሱን ጠቁመዋል፡፡

እንደርሳቸው ገለጻ፤ በሁለት ሺህ 672 ዜጎች ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረሱንም ነው የገለጹት። የትራፊክ አደጋው በንብረት ላይ አንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ኪሳራ አድርሷል ብለዋል፡፡

በተደረጉ ጥናቶች ከ60 በመቶ በላይ የትራፊክ አደጋዎች የሚደርሱት በአሽከርካሪዎች ምክንያት ሲሆን፤ ከ20 በመቶ ያላነሱት ደግሞ በተሽከርካሪዎች ብቃት ማነስ መሆኑን መረጃዎች እንደሚጠቁሙም ነው የገለጹት፡፡ በመሆኑም መንግሥት ሁለቱን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡



አቶ ፍቃዱ ደምሴ

# ነፃ የሕግ አገልግሎትን ማጠናከር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እየተዘጋጀ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በመላ ሀገሪቷ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን ማጠናከር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እያዘጋጀ መሆኑን የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የጠበቆች አስተዳደርና የነፃ ሕግ ድጋፍ አገልግሎት ዳይሬክተር ፍቃዱ ደምሴ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እኩል የፍትህ ተጠቃሚነትና ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚሰጥ አገልግሎት በመሆኑ ተገቢው የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልገዋል።

በዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ የነፃ የሕግ ድጋፍ ስትራቴጂ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መጽደቁንና ይህም ክፍተቶቹን በመዳሰስ መፍትሔዎች ያስቀመጠ መሆኑን አመላክተዋል።

ስትራቴጂው ሁሉንም ክፍተቶች የማይፈታ በመሆኑ ሚኒስቴሩ የሕግ ማዕቀፍ እያዘጋጀ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

ሚኒስቴሩ የሚያዘጋጀው የሕግ ማዕቀፍ በስትራቴጂው ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን የሚመለከትና በዝርዝር ያልተዳሰሱ የነፃ የሕግ ድጋፍ ጉዳዮችን በግልጽ የሚያብራራና መፍትሔ የሚሰጥ መሆኑን አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያም ፍትህ ሚኒስቴር የጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች፣ የጠበቃ ድርጅቶች፣ በፍትህ ሚኒስቴርና በፍርድ ቤት ያሉ ተከላካይ ጠበቆች፣ የሕግ መምህራን እንዲሁም ፍቃደኛ የሆኑ የሕግ ተማሪዎች የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ዜጎች ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል ብለዋል።

አገልግሎቱ ላይ የተደራሽነት ችግሮች መኖራቸውን ተናግረው፤ የነፃ ሕግ ድጋፍ አገልግሎቱን በአብዛኛው በገጠሪቱ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ ዜጎች የሚፈልጉት ቢሆንም በርካታ ጠበቆች የሚገኙት በከተማ አካባቢ በመሆኑ ሰፊ ተግዳሮት መፍጠሩን አንዱ ተግዳሮት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አገልግሎቱን የሚያገኙ ማኅበረሰቦች ለጠበቃ የመክፈል አቅም የሌላቸው እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ፍርድ ቤቶች ከክፍያ ነፃ በሆነ መንገድ ጠበቃ እንዲያገኙ የሚልኳቸው ሰዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ አገልግሎቱን በሚፈለገው ልክ በመላ ሀገሪቷ ለማዳረስ የሚያጋጥመውን ክፍተት የሚሸፍን የሕግ ማዕቀፍ እንደሚዘጋጅ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ክልሎች ላይ ከወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ክልልና ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚመሩ ጉዳዮች ላይ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎቱን ከማቅረብ አኳይ በቅንጅት የመሥራት ችግር አለ ብለዋል።

ከወረዳ እስከ ፌዴራል ፍርድ ቤት ድረስ የሚታዩ ጉዳዮች ላይ የጥብቅና አገልግሎቱን በነፃ መስጠት ቢቻልም ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች መሸፈን የሚቻልበት አግባብ ባለመኖሩ የሚሰጠው አገልግሎት የተሟላ እንደማይሆን ተናግረዋል።

አሁን ላይ እየተዘጋጀ የሚገኘው የሕግ ማዕቀፍ ተመሳሳይ ችግሮችንና ሌሎች ክፍተቶችን ለመሸፈን የሚረዳ በመሆኑ በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎቱ የሚመለከታቸው አካላት የየራሳቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየተሠራ መሆኑ አስታውቀዋል።

# የኢትዮጵያና የኬንያ መሪዎች ውይይት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሁለቱ መሪዎች የሁለቱን ሀገራት ጥልቅ እና ታሪካዊ ግንኙነት ብሎም ኢኮኖሚያዊ ትስስር አውስተው፤ ይኸንኑ በቁርጠኝነት ማጠናከር እንደሚገባ መስማማታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መረጃ ያመላክታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክትም ወንድሜ ፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ በኬንያ ላደረጉልን ደማቅ አቀባበል አመሰግናለሁ። ሰፋ ያሉ ጉዳዮችን ያካተተው ውይይታችን የቆየውን ትስስራችንን ያጠናከረ ብቻ ሳይሆን የወደፊት ቁልፍ የትብብር መስኮችንም የለየ ነበር። የጋራ አንድ ርዕይ እና ዕጣፈንታ እንዳላቸው ጎረቤቶች በጋራ ለመሥራት ያለን ቁርጠኝነት ተጠናክሯል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከኬንያው ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ጋር በመሆን የሱስዋን ንዑስ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያ ጎብኝተዋል።

የሱስዋ ኤሌክትሪክ ጣቢያ ኢትዮጵያን ከኬንያ ያስተሳሰረ ፕሮጀክት ሲሆን በኬንያ ካጂያዶ ግዛት የሚገኝ ነው።

# ከ40 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ጤና...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አድሰዋል።

ዘንድሮ የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በሀገር አቀፍ ደረጃ 60 ሚሊዮን አባላት ለማድረስ መታቀዱን ገልጸው፤ በተያዘው በጀት ዓመት አምስት ሚሊዮን ዜጎች ለመመዝገብ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በአዋጁ መሠረት የጤና መድህን አገልግሎት የአባላት ምዝገባ ጊዜ ጥርና የካቲት ወር መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ አሁን ላይ የምዝገባ ሥራው እስከ የካቲት መጨረሻ ባለው ጊዜ በዘመቻ መልክ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የአባላት ምዝገባው በአፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉልና ሶማሌ ክልሎች ላይ አለመጠናቀቁን ጠቅሰው፤ በቀሪ ጊዜያት እቅዱን ለማሳካት እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

አማራ ክልል ባጋጠመው የሰላም ችግር ምክንያት ሥራው በሚፈለግው ደረጃ እየተከናወነ አለመሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ አዲስ አበባ፣ ሐረሪ፣ ማዕከላዊ ኢትየጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማን



አቶ ጉደታ አበበ

ጨምሮ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልልና ኦሮሚያ ክልል ከተወሰኑ አካባቢዎች ውጪ አፈጻጸማቸው ከ70 በመቶ በላይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የጤና መድህን ሥርዓት ዜጎች በሚከፍሉት መዋጮ የጤና እክል በሚያጋጥማቸው ወቅት ያለምንም የክፍያ ስጋት የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑን አስገንዝበው፤ አካታችና ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳካት እንደሚረዳ ገልጸዋል።

የአባልነት ክፍያ የመክፈል አቅም የሌላቸው 10 ሚሊዮን አርሶ አደሮች ዓመታዊ መዋጯቸው በመንግሥት የተሸፈነላቸው መሆኑን በመግለጽ፤ ይህም ለሕክምና ያላቸውን እንስሳት በመሸጥ ለከፍተኛ ወጪ እንዳይዳረጉ ማድረጉን ገልጸዋል።

በመደበኛው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የማኅበራዊ ጤና መድህን አገልግሎትን ለማስጀመር የዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው ብለዋል፡፡

የጤና መድህን ሥርዓት በጤናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ለውጥ እያስገኘ በመሆኑ ጠቅሰው፤ በቀጣይ ጊዜያት ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል የጤና መድህን ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አቶ ጉደታ መልዕክታቸውን አስላልፈዋል።

# 128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ክብሩን ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴዎች ባቀረቡት ሪፖርትም የዓድዋ ጀግኖችን የሚዘክር የ34 ደቂቃ ዶክመንታሪ ፊልም፣ ቢል ቦርድ፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ሎጎ፣ መሪ ቃል እና ሠራዊቱ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ሆኖ የሚወያይበት ጽሑፍ መዘጋጀቱን ገልፀዋል።

በዕለቱም የካቲት 23 ቀን ወታደራዊ የሰልፍ ትርኢት እና ድሉን የሚያስታውሱ ልዩ ልዩ ትርኢቶች ፒያሳ በሚገኘው የዓድዋ ድል መታሰቢያ እንደሚቀርብ የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴዎች ማሳወቃቸውን ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ገጽ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮ- ኬንያ አዲስ የግንኙነት ምዕራፍ የላቀ የጋራ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ነው

የኢትዮጵያ እና የኬንያ ሕዝቦች ግንኙነት ከጉርብትና ባለፈ ዘመናትን በሰላምና በወዳጅነት መንፈስ መዳዝ የቻለ ነው። መተማመንና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ መሠረት ያደረገው የሀገራቱ ግንኙነት ሁሉን አቀፍ እና በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ መዋዥቅ ሳይታይበት ለረዥም ዓመታት የዘለቀ ነው።

የሀገራቱ ሕዝቦች ድንበር ከመጋራት ባለፈ፤ በባህል፣ በቋንቋ እና በታሪክ የተሳሰረ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ታሪክ ባለቤት ናቸው፤ ይህም ክፉ ጊዜያትን ሳይቀር በወዳጅነት እንዲያሳልፉ አቅም ሆኗቸዋል። በቀጣናው ለሚገኙ ሀገራት ሕዝቦች የመልካም ጉርብትና ተምሳሌት እንዲሆኑም አስችሏቸዋል።

በበጎ ህሊና እና በአፍሪካዊ የወንድማማችነት መንፈስ ላይ የተመሠረተው የሁለቱ ሀገራት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነት፤ የሀገራቱን ሕዝቦች ወዳጅነትና የጋራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ዛሬ ላይ ወደ አዲስ ታሪካዊ ምዕራፍ እየተሸጋገረ ይገኛል።

ሀገራቱ አሁን ላይ የጀመሩት አዲስ ታሪካዊ የግንኙነት ምዕራፍ የሀገራቱ ሕዝቦች ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካ መስተጋብሮችን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር፤ የዜጎቻቸውን የጋራ ነገዎች ብሩህ ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂክ አቅም በመገንባት ረገድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ።

ካለንበት ወቅት፤ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ እውነታ አኳያም፤ ሀገራቱ ግንኙነታቸውን በሁለንተናዊ መንገድ ለማጠናከር የጀመሩት መንገድና ጉዞ፤ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን በጋራ መቋቋም የሚያስችል አቅም ለመፍጠር የተሻለ ዕድል የሚፈጥርላቸው ነው። ከዚህም ባለፈ ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን በተሻለ መንገድ ለማስከበር ትልቅ አቅም ይሆናቸዋል።

ሀገራቱ በቅርቡ በአዲስ አበባ ባካሄዱት 36ኛው የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ እና በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ የተደረሰበት ስምምነትም የሀገራቱን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ፤ የሀገራቱን ሕዝቦች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያሳድግ እንደሆነም ይታመናል።

ስምምነቱ በሀገራቱ መካከል የቆየውን ጠንካራ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በሁሉም መልኩ በላቀ ደረጃ ማስቀጠል የሚያስችል፤ በውጭ ጉዳይና መከላከያ ዘርፎች፣ በንግድና ኢንቨስትመንት፤ በማኅበራት ዘርፎች ለጋራ ተጠቃሚነት አብረው መሥራት የሚያስችላቸውን ዕድል የሚፈጥር ነው።

በተለይም አሁን ባለንበት ዓለም አቀፋዊ እውነታ፤ ሀገራት ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ ከተናጠል ይልቅ በጋራ መንቀሳቀስ እንደ ዋነኛ ስትራቴጂ እየተወሰደ ባለበት ሁኔታ፤ በሀገራቱ መካከል እየታየ ያለው አዲስ የትብብር ግንኙነት ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ የሚረዳ ነው።

የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሕዝቦች ሰላምና ልማት ለማስፈን ካለባቸው ተግዳሮቶች አንጻር፤ የሀገራቱ የጀመሩት አዲስ ታሪካዊ የትብብር ግንኙነት በአካባቢው ዘላቂ ሰላም እና ልማት ለማስፈን አስፈላጊ የሆነውን የመተማመን መንፈስ ለመፍጠር ይረዳል። የቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች በሁለንተናዊ መልኩ የጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ተጨባጭ ተሞክሮ መፍጠር ያስችላል፡፡

በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት አካባቢያዊ ጸጋዎችን በጋራ በማልማት፤ የጋራ ተጠቃሚነትን በቀጣናው ሕዝቦች መካከል ለማስፈን ለጀመሩት ዘመኑን የሚዋጅ እሳቤ ስኬት የሚኖረው ጠቀሜታ ከሁሉም በላይ የላቀ ነው። ወደ ፊት ለቀጣናው ሀገራት ሕዝቦችም ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ነው።

የሀገራቱ በበጎ ህሊና እና በአፍሪካዊ የወንድማማችነት መንፈስ ላይ የተመሠረተውን የቆየ ግንኙነታቸውን በማደስ የጀመሩት አዲስ ግንኙነት በግጭት፣ በድህነትና በኋላ ቀርነት ለዘመናት ዋጋ ሲከፍል ለቆየው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ፤ አዲስ የብስራት ድምጽ ሆኖ ሊሰማ የሚችል ዘመኑን የሚዋጅና ትውልድ ተሻጋሪ እንደሚሆንም ይታመናል።

ለዚህ ደግሞ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ከበዓለ ሲመታቸው ማግስት በምሥራቅ አፍሪካ የመጀመሪያ የተባለለትን ይፋዊ የሥራ ጉብኝታቸውን ከኢትዮጵያ መጀመራቸውም ሆነ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ለሁለት ቀናት መንግሥታዊ ጉብኝት ኬንያ ሲደርሱ በጆሞ ኬንያታ አውሮፕላን ጣቢያ በፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ የተደረገላቸው ደማቅ አቀባበል፤ በቆይታቸው ያደረጓቸው ውይይቶችና በውይይቶቹ የተደረሰባቸው ስምምነቶች የዚሁ ታሪካዊ እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አሳሳቢው የአበረታች መድኃኒቶች ተጠቃሚነት ጉዳይ

ብርሃን ፈይሳ

የስፖርቱን ዓለም ከሚያደፈርሱና ንጹህ የውድድር መድረኮችን ከሚያራክሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ የስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ጉዳይ ነው። የማይገባ ዝና ለማግኘት በሚደረግ አቋራጭ መንገድ በጥረታቸው ጠንካራ ተፎካካሪ የሆኑ ስፖርተኞችን ዕድል ከመዝጋት ባለፈ የስፖርት ተአማኒነትንም ገደል ይከታል።

የትኛውም ስፖርተኛና ባለሙያ አውቆም ይሁን ሳያውቅ አበረታች ቅመም ተጠቅሞ ሲገኝ፣ እንዲጠቀም ሲያደርግ ወይም መሰል ተግባር ላይ መሳተፉ ከተረጋገጠ ያገኛቸው ስኬቶችና ክብሮችን ተነጥቆ በጊዜያዊነት እንዲታገድ ከዚያም ለሕይወት ዘመን ከስፖርት ዓለም እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

ብርቱ ጥረትና ጽናትን በሚጠይቀው የስፖርተኝነት ሕይወት በአቋራጭ ለመጠቀም የተለየ ብቃት የሚጨምርላቸውን ዘዴዎችን መጠቀም ከጥንት አንስቶ ሲተገበር የቆየ ተግባር መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ግሪካውያን፣ ግብጾች፣ የእንግሊዝና መሰል ሀገራት በኦሊምፒክ የሚሳተፉ አትሌቶቻቸውን ለማበርታት የተለያዩ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ዘዴዎችን ይጠቀሙ ነበር።

ይህ ሁኔታ ከዘመኑ ጋር እየዘመነና እየረቀቀ መጥቶ ሰው ሠራሽ የሆኑ ቅመሞችንና ፈሳሾችን በተለያዩ መንገዶች ወደ ሰውነት በማስገባት በተፈጥሮ የተቸሩትን ብቃትና በዘመናዊ ሥልጠና ያገኙትን ሁለንተናዊ አቅም በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር ውጤታማ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ይስተዋላል።

የስፖርት አበረታች ቅመሞቹ በእንክብል፣ በመርፌ፣ በምግብ፣ በሰውነት ውስጥ በሚቀበር እንዲሁም በግሉኮስ በደም ስር የሚሰጡ ሲሆን፤ ሳይንሳዊ ሂደትን ተከትለው የሚካሄዱና በጥንቃቄ ተግባር ላይ የሚውሉ መሆናቸውን ተከትሎም በምርመራ መረዳት አዳጋች የሚሆንበት ወቅት ይኖራል።

ይህ የንጹህ ስፖርት እና ሃቀኛ ስፖርተኞች ጸር የሆነ ጉዳይ ከግለሰብ እስከ ሀገር የሚከወን መሆኑ ደግሞ ነገሩን ይበልጥ ያወሳስበዋል። ከየትኛውም ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድር የታገደችው ሩሲያ ለዚህ ዋነኛ ምሳሌ ስትሆን፤ በስፖርቱ ዓለም ታላላቅ ክብሮችን መቀዳጀት የቻሉ ምርጥ አትሌቶች፣ ዓለም አቀፍ የስፖርት ማኅበራት አስተዳዳሪዎች እና አሰልጣኞች ቀድሞ የነበሩበት የስኬትና የክብር ማማ ከመሠረቱ ተናግቷል።

በግለሰቦች ምክንያትም ሀገራት ስማቸው በአሉታዊ መንገድ መነሳቱ እጅግ የሚያስቆጭ መሆኑ አያጠያይቅም። ተጠቃሚነቱ እግር ኳስን ጨምሮ በሌሎች ስፖርቶች ላይ ስለመኖሩ አመላካች ፍንጮች ይኑሩ እንጂ፤ በከፍተኛ ሁኔታ ስር የሰደደው ግን በአትሌቲክስ ስፖርቶች መሆኑ ከስፖርት ቤተሰቡ የተደበቀ አይደለም።

በአትሌቲክስ ስፖርት በበጎ ስሟን የገነባችው ኢትዮጵያም ከዚህ አደገኛ ጉዳይ ጋር ስሟ መነሳት ከጀመረ ዓመታትን ተሻግሯል። ተፈጥሮ ባደላት መልከዓ ምድር እና የአየር ሁኔታ ንጹህ ላባቸውን በሚያፈሱ አትሌቶቿ ስሟ ለዘመናት በድል ሲነሳ ኖሯል፡፡

ከ2010 ዓ.ም አንስቶ ግን ባልተጠበቀ ሁኔታ የአትሌቶች አበረታች ንጥረ ነገር ተጠቃሚነት ምልክቶች በመኖራቸው የዓለም አቀፉ የጸረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ትኩረት ከሚያደርግባቸው ሀገራት መካከል ልትመዘገብ ችላለች። ይህም በጥቂት አትሌቶች ተጠቃሚነት በተግባር ሊረጋገጥ በመቻሉ ሀገር አቀፍ የጸረ አበረታች ቅመሞች ንቅናቄ ተፈጥሮ ነበር። ከ2011ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ደግሞ ሦስት ሦስት አትሌቶች ተጠቃሚ መሆናቸው መረጋገጡን ተከትሎ፤ ቁጥሩ እንደ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቢሆንም ከሌላው ዓለም አንጻር ከስጋት ቀጣና ሊወጣ ችሎ ነበር።

ነገር ግን ካለፈው ዓመት አንስቶ በአትሌቶች ዘንድ ያለው የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት በድጋሚ እያንሰራራ በመምጣት አሁን ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ ሊባል ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ነገሩን ይበልጥ አስከፊ የሚያደርገው ደግሞ በወጣትና ተተኪ አትሌቶች ዘንድ በስፋት መስተዋሉ ነው።

በ2015 ዓ.ም ከተያዙ የቅመሙ ተጠቃሚ አትሌቶች መካከል 11 የሚሆኑት ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ቻምፒዮናዎች ላይ የተሳተፉ ሲሆኑ፤ ይህም ተተኪ አትሌቶች ላይ የተደቀነውን አደጋ በግልጽ የሚያመላክት ነው። በተለያዩ የውጭ ሀገራት በሚካሄዱ ውድድሮች ላይ ተሳትፈው የሚደረግላቸውን ምርመራ ማለፍ የማይችሉ ታዋቂ አትሌቶች ቁጥርም በተመሳሳይ እያሻቀበ ይገኛል።

በዚህም ኢትዮጵያ በድጋሚ እንደ ጎረቤት ሀገር ኬንያ፣ ሩሲያ እና ዩክሬን በዓለም አቀፉ ተቋም በዓይነ ቁራኛ ከመታየት እንዳትላቀቅ አድርጓታል። ይህም እጅግ ጠንካራ ሥራ በማከናወን የተመሰከረለትንና ለሌሎች ሀገራትም ተምሳሌት የነበረው የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣንን ተግባር ጥያቄ ውስጥ የሚከትና ፌዴሬሽኑንም ስጋት ላይ የሚጥል ሆኗል።

በመሆኑም ተቋማቱ የአደጋ ጊዜ ደውሉን በመጫን ሁኔታው ከአቅማቸው በላይ መሆኑንና መንግሥትም እጁን እንዲያስገባ ጠይቀዋል። ከግለሰብ አንስቶ እስከ መንግሥት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ በመሆኑ ከምንጩ አጣርቶ የማያዳግም መፍትሔ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም። የአትሌቶች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ቁጥጥሩን አዳጋች ሲያደርገው የግንዛቤ ማነስ ዋነኛው ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይጠቀሳል።

ይሁንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገርን እስከመወከል የደረሱ አትሌቶች ስማቸው ከዚሁ ጋር መያያዙ ግን እውነታውን አንጻራዊ ያደርገዋል። በማናጀሮች መሰልጠን መስፋፋት፣ የውጭ ሀገራት ሰልጣኞችን (የሌላ ሀገራት ዜጎች) ጨምሮ ማንነታቸው የማይታወቁ አትሌቶች እንቅስቃሴ፣ በአትሌቶች ዘንድ እያደገ የመጣው የተለያዩ ቫይታሚኖችን የመጠቀም ዝንባሌ፣ መድኃኒት መደብሮች የተከለከሉ አበረታች ንጥረ ነገሮችን በውስጣቸው የያዙ መድኃኒቶችን ያለማዘዣ በቀላሉ መሸጣቸው፣ በሀገር ውስጥ ምርመራውን ማድረግ የሚችል ቤተሙከራ ባለመኖሩ በሚፈለገው ልክ የአትሌቶችን ናሙና መውሰድ አለመቻል፣ ተጠቃሚነታቸው የተደረሰበት አትሌቶች የላላ የቅጣት ሥርዓት፣... የመሳሰሉ ጉዳዮች ሁኔታው እንዲስፋፋ ምክንያቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ሰኔ 30/1999 ዓ.ም በልዩ ስብሰባ በአዋጅ ቁጥር 554/1999 በዩኔስኮ የጸደቀውን የጸረ አበረታች ቅመሞች ኮንቬንሽን ተቀብላ አጽድቃለች። ኮንቬንሽኑ 7 ክፍሎችና 43 አንቀጾችን የሚያጠቃልል ነው። በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 526 ላይም አበረታች መድኃኒትን የተመለከተ ሕግ ተቀምጧል። በዚህም መሠረት አበረታች መድኃኒቱን ያመረተ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ፣ የሸጠ፣ በባለሙያነት ያዘዘ፣ ያከፋፈለ እንዲሁም በሕገወጥ መንገድ የተጠቀመና ሌላ ሰው እንዲጠቀም ያደረገ በቀላል እስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ከባድ ጉዳት ካስከተለ ደግሞ በ5ዓመት ጽኑ እስራት የሚቀጣ ይሆናል ይላል። ይሁንና ከሀገር ክህደት የማይተናነሰው ይህ ተግባር በስፖርት ማኅበራቱ በሚጣል የዓመታት እገዳ ከመታለፍ ባለፈ በወንጀለኝነት ተጠይቀው እርምጃ የመውሰዱ ሁኔታ አለመለመዱ ስፖርተኞቹ ራሳቸውን እንዳያቅቡ ሳያደርጋቸው እንዳልቀረ ይታመናል።

ሻምበል አበበ ቢቂላ ከቀዶ ጥገና መልስ በመሮጥ፣ ዋሚ ቢራቱ ውስጥ እግራቸው እየደማ በመወዳደር፣ ቀነኒሳ በቀለ እና ኀተይቶም ገብረሥላሴ በቅጡ ከኀዘናቸው ሳያገግሙ በዓለም አደባባይ በመወከል፣ ጥሩነሽ ዲባባ ሕመሟን ተቋቁማ በማሸነፍ፣ ጉዳፍ ጸጋይ እና ያለምዘርፍ የኋላው በጽናት በመዋደቅ፣ ሙክታር እድሪስ ከሕክምና መልስ ለአሯሯጭነት ገብቶ የወርቅ ባለቤት በማድረግ፣ ገብረእግዚአብሔር ገብረማርያም፣ ስለሺ ስህን፣ ወርቅነሽ ኪዳኔ... የወርቅ ሜዳሊያ ሳያሳሳቸው አሳልፈው በመስጠት፣ ... መስዋዕትነትን የከፈሉት ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ክብር ነው።

ለሀገር ላብ ብቻ ሳይሆን ደምም እንደሚፈስላት ያስተማሩን አንጋፎች በተወሰኑ ኃላፊነት የጎደላቸው ግለሰቦች አሳፋሪ ተግባር ፈጽሞ ገድላቸው ሊጎድፍ አይገባምና አትሌቲክስን የሕይወት መንገዳቸው ያደረጉ ሁሉ ወርቃማውን ታሪካችንን ሊያበላሹ አይገባም፡፡

የስፖርት ተቋማትና ባለሙያዎች ኃላፊነት ብቻም አይደለምና የሚመለከታቸው ሁሉ እጃቸውን ከደሙ ሊያነፁ ይገባል። ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንስቶ የጤና ሚኒስትር፣ ትምህርት ሚኒስትር፣ የፍትህ አካላት፣ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፣ ... የስፖርት አበረታች ቅመሞችን ጉዳያቸው አድርገው ስለ ኢትዮጵያ ክብር የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት ትልቅ መሆኑን ተረድተው በዚያ ልክ ሊሠሩ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ

# በዓሉን የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን በሚመጥን ደረጃ ማክበር ይጠበቅብናል

**በቴዎድሮስ ደርጋ**

ከቀናት በኋላ ታላቁ የአፍሪካውያን ብሎም የጥቁር ሕዝቦች ድል የሆነው የዓድዋ በዓል በአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ይከበራል። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ጥቂት የማንባል አያቶቻችን የሰሩትን ታላቅ ገድል በአግባቡ ማወደስ አቅቶን፤ በበዓሉ አከባበር ዙሪያ ለብሽሽቅና ለስድድብ ቃላት በመምረጥ ስንደክም መታየታችን አንገት የሚያስደፋ ነው።

በመሰረቱ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ክብረ በዓል አከባበር በራሱ ከተጀመረ አንስቶ ወጥነት ባለው መልኩ ሲከበር አልነበረም። ብዙዎቻችን ይህንን ባለማወቃችን ይመስለኛል ሁሌም አዲስ ነገር እንደተፈጠረ ሁሉ በዓመት ለዚያውም ለግማሽ ቀን ለማይሞላ መርሃ ግብር አገር ይያዝ የምንለው። ለዛሬ ጽሁፌም የዓድዋ በዓል እንዲህ ተደርጎ፤ እዚህ ተኩኖ፤ በዚህ መልኩ ብቻ መከበር አለበት ለሚሉ ከዚህ በፊት የነበረውን አካሄድ መረጃ ጠቅሼ ለማቅረብ ወደድኩ።

መረጃውን የማጋራችሁ የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት 127 ኛውን የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓልን ምክንያት በማድረግ «የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓል አከባበር ታሪክ» በሚል ከተዘጋጀ በራሪ ወቀረቀት ነው። ጽሁፉን ለማዘጋጀት "Memories of the victory of Adwa: A focus on its commemoration (1941- 1999)" በሚል በ2004 በቢንያም ወልደ ገብርኤል የተዘጋጀውን የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት ጽሁፍ መጠቀማቸውንም አስቀምጠዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ለመጀመሪያ ግዜ በይፋ የተከበረው ጦርነቱ በተካሄደ በሰባተኛው ዓመት በ1895 ዓ.ም በቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ነው። በበዓሉ ሁሉም ሀገረ ገዢዎች ጦራቸውን ይዘው ተገኝተዋል። ዳግማዊ ምንሊክ 8000 ሺ ፍሪዳ ጥለው ለ60ሺ ሰዎች ግብር አብልተዋል። 307 ሺ ወታደሮችም ወታደራዊ ትርኢት አሳይተዋል፤ ንጉሱ በየዓመቱ የካቲት ሀያ ሶስት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ዕለት ሆኖ እንዲከበር አውጀዋል። ለምን ለማክበር እንዳሰቡ ሲገልጹም " ፈጣሪ በሰላምና በጤና ጠብቆ ሰባት ዓመት ስላቆየን [ዕለቱን] ላከብረው አቅጂያለሁ። የማከብረው ግን ለጉራ እና ያለኝን ጦርና መሳሪያ ለማሳየት አይደለም ።" የአማርኛ ትርጉም በአዘጋጆቹ።

ከ1895ቱ መታሰቢያ በዓል በኋላ እስከ 1917 ዓ.ም በነበሩት ዓመታት በዓሉ በምን መልኩ ይከበር እንደነበር ዝርዝር መረጃ የለም። ያም ሆኖ ግን በየዓመቱ በደበዘዘ መልኩም ቢሆን መከበሩን ቀጥሏል። ይከበር የነበረው በጊዮርጊስ ካቴድራል ነበር። ከ1917 እስከ 1920ዎቹ በዚህ ዘመን ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና አልጋ ወራሽ ተፈሪም በበዓሉ ይታደሙ ነበር። በዕለቱ ሥራ ይዘጋል፤ አዲስ አበባም በሰንደቅ ዓላማ ታሸበርቃለች፤ ቀሳውስቱ በዋዜማው ሲቀድሱና ሲፀልዩ ያድራሉ። የ1917 በዓል (29ኛው ዓመተ በዓል) በጣም ደማቅና የምንሊክና የራስ መኮንን ፎቶ ለእይታ እንዲቀርብ ተደርጎ በቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ተከብሯል።

ከጣሊያን ዳግም ወረራ በፊት የመታሰቢያ በዓላቱ ሲከበሩ ስለጦርነቱም ሆነ ስለድሉ ዝርዝር ዘገባ በጋዜጦች አይዘገብም ነበር። (በ1928 እ.ኤ.አ በኢትዮጵያና በጣልያን መካከል በተፈረመው የወዳጅነት ስምምነት የተጀመረውን መልካም ግንኙነት ላለማደናቀፍ)። ከ1922 ቱ ክብረ በዓል ቀደም ብሎ የዳግማዊ ምንሊክ ሀውልት ተመርቆ እንዲከፈት ተደርጓል። የ1923 ቱን የመታሰቢያ በዓል በሚመለከት በእለቱ ዜና በጋዜጣ አልተሰራም።

እአአ የ1934ቱ የወልወል ግጭት በቀጣይ ዓመታት የነበሩ የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓላት በድምቀት እንዲከበሩ አስተዋጽኦ አድርጓል። በጋዜጦችም ለይ የአድዋን ድል አጉልቶና አስፋፍቶ መጻፍ የአድዋ ጀግኖቻችን ማወደስ እና በተቃራኒው ጣልያንን መተቸት እና መንቀፍ ተጀመረ። ከወረራው በፊት የነበረው የመጨረሻው (የ1927ቱ የመታሰቢያ በዓል በአደባባይ በቀረቡ የጀግንነት ግጥሞች ፉከራና ሽለላ እጅግ በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል። ነገር ግን በበዓሉ ላይ ብዙ ሕዝብ አልታደመም ምክንያቱም መዋጋት የሚችለው ሰው ሁሉ ወደጦር ግንባር በመዝመቱ ነው።

ዘመነ ጣልያን ጣልያኖች አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በተለይ ከዳግማዊ ምንሊክ ታሪክ ጋር የተገናኙ ነገሮችን አውድመዋል። ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ከልክለው ነበር። በመሆኑም ጣልያን በኢትዮጵያ በቆየችባቸው አምስት ዓመታት የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል አልተከበረም።

ከነጻነት መልስ (1933 እስከ 1966 ዓ.ም ) የነበረው አከባበር፤ በ1933 ዓ.ም የዓድዋ መታሰቢያ በዓል ለመጀመሪያ ግዜ የሕዝብ በዓል ሆኖ እንዲከበር በሕግ ተደነገገ። በዓሉን ከሃይማኖታዊ ይዘት ማላቀቅ ስላልተቻለ በቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድደራል በጸሎትና በቅዳሴ መከበሩንም ቀጠለ። በእነዚህ ዓመታት በዓሉ መከበሩን ቢቀጥልም የሚያዚያ 27 የመታሰቢያ በዓል " ማጀቢያ" ሆኖ እንደቆየ የሚገልጹ አሉ።

ለምሳሌ ጋዜጦች በእለቱ ስለ ዓድዋ ድል ቢጽፉም በጽሁፋቸው ግን ዓድዋን ሳይሆን ሚያዚያ 27ን ማጉላትና ለአርበኞች ትግል ትኩረት ሰጥቶ መጻፍ ይንጸባረቅ ነበር። በዓሉ ከ1943 ዓ.ም ጀምሮ በማርሽ ባንድ መታጀብ ጀመረ፤ 21 ግዜም መድፍ ይተኮሳል። ንጉሱ ንግስቲቱና መኳንንቱ ይሳተፋሉ። ንጉሱ በማይኖሩበት አጋጣሚ አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ይገኛሉ።

የ1963 ቱ የመታሰቢያ በዓል (75ኛ በዓል) ልዩ ነበር። ይህም ለመጀመሪያ ግዜ የአበባ ጉንጉን የማስቀመጥ ስነስርዓት በመጀመሩ ከድል በኋላ ለመጀመሪያ ግዜ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ግብር ማብላታቸው እና ለመጀመሪያ ግዜ በቀጥታ ከድሉ ጋር ያልተገናኘ ("የአድዋ መንፈስ በሌሎች መስኮችም ድል እንድናደርግ ማገልገል አለበት " የሚል) መልዕክት እንዲኖረው በመደረጉ ነው።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ክብረ በዓል በደርግ ዘመን 1966 እአሰከ 1983 ዓ.ም፤ የደርግ መንግስት ስልጣን እንደያዘ ሚያዚያ 27 ወደ መጋቢት 28 ተዛውሮ እንዲከበር የዓድዋ የመታሰቢያ በዓል ባለበት እንዲቀጥል በድሉ ስም ጎዳና (የዓድዋ ጎዳና) እንዲሰየምና በዓድዋ ጀግኖች ስም ጎዳና እንዲሰየም ተደረገ። በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በበዓሉ ቀን የተለያዩ ትርኢቶችን ማቅረብ ተጀመረ።

ለመጀመሪያ ግዜ ድሉ ሙሉ በሙሉ አለማዊ ይዘትና ትርጉም ኖሮት እንዲከበር ተደረገ ቦታውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ወደ ምንሊክ አደባባይ ተዛወረ። የአበባ ጉንጉን ማስቀመጥና የመታሰቢያ ንግግር ማድረግ የበዓሉ ዋና ድምቀት ሆኑ። በየዓመቱ የተለያዩ ወቅታዊ የሆኑ ነገሮችን የሚመለከቱ መሪ መልእክቶች ይለጠፉበትም ነበር።

ከ1967 እስከ 1974 ዓ.ም ባለው ግዜ በዓሉ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በድምቀት ይከበር ነበር። ከ1974 እስከ 1983 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ግን ድምቀቱ ቀንሷል። ይህም የደርግ መንግስት ተቃውሞ እየበዛበት በመምጣቱ እንደ ሊቀመንበሩ ያሉ የበዓሉ የክብር ታዳሚዎች ቀርተው በበታች የስራ ኃላፊዎች እንዲፈጸም በመደረጉ ይቀርቡ የነበሩት ትርኢቶችም እንዲቀሩ በመደረጉ ነው። በ1968፤ 1970 እና 1972 ዓ.ም የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓል በመስቀል አደባባይ እንዲከበር ተደርጓል። የ1967ቱ ክብረ በዓል ከፍተኛ ሕዝብ የተሳተፈበት ሳይሆን እንዳልቀረ ተዘግቧል።

ድህረ 1983 ዓ.ም የነበረው የአድዋ ድል አከባበር ከፍተኛ የሀሳብ መለያየት የታየበት ነው። በዘመነ ኢሕአዴግ የተከበረው የመጀመሪያው ክብረ በዓል (1984 ዓ.ም) የምንሊክ ሀውልት "ይፍረስ" እና "መፍረስ የለበትም" የሚሉ ሁለት ተቃራኒ ተቃዋሚ ሰልፎች ከተካሄዱ በኋላ በመስቀል አደባባይ እንዲከበር ተደርጓል። በሀሳብ የመለያየትና የመወዛገቡ ነገር እስካሁን የቀጠለ ሲሆን በተለይ በ1988ቱ የ100ኛ ዓመት የመታሰቢያ በዓል (centenary) አከባበር ሂደት በስፋት ተስተውሎ ነበር።

> **የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ለመጀመሪያ ግዜ በይፋ የተከበረው ጦርነቱ በተካሄደ በሰባተኛው ዓመት በ1895 ዓ.ም በቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ነው። በበዓሉ ሁሉም ሀገረ ገዢዎች ጦራቸውን ይዘው ተገኝተዋል**

በ1984ቱ በዓል ለይ የአዲስ አበባ ጊዚያዊ አስተዳደር የነበሩት አቶ ሙሉዓለም አበበ ምንሊክ አደባባይ በመገኘት የአበባ ጉንጉን ያስሰቀመጡ ሲሆን «የዓድዋ ድል የአንድ ግለሰብ ድል ወይም በጥቂት የጦር መሪዎች የተገኘ ድል ሳይሆን በብሄር- ብሄረሰቦች የተገኘ » ድል እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህ ዓመት ለበዓሉ መድፍ የተተኮሰው 12 ግዜ ብቻ ነበር።

ለ100 ኛ ዓመት የመታሰቢያ በዓል (centenary) መንግስት የራሱን ትርጉምና መልእክት ይዞ የመጣ ሲሆን በተለይ ደግሞ ድሉ " የአፍሪካ ድል" ሆኖ እንዲታይ ከፍተኛ ትኩረትና ጥረት ተደርጓል። በዓሉን ለማክበር የተቋቋሙት ሶስት ኮሚቴዎች በየራሳቸው መንገድ ይንቀሳቀሱና ከፍተኛ ውዝግብ እና መካሰስ ውስጥ ገብተው ነበር። የታሰበውን አከባበር በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ የተደረገ ሲሆን በዓሉም በምንሊክ አደባባይ ሳይሆን መገናኛ አካባቢ ባለ አደባበይ ተከብሯል። እ.ኤ.አ የ1991ዱን የኤርትራ ወረራ ተከትሎ በዓሉን በድምቀት ለማክበር ተሞክሯል። በኢሕአዴግ ዘመን ከተከበሩት የዓአድዋ ድል የመታሰቢያ በዓላት መካከል በጣም ደማቅ የነበረው የ1991 ዓ.ም ነው። (መከላከያ ሰራዊት ባድሜን ከኤርትራ ነጻ ከማውጣቱ ጋር በመገጣጠሙ)።

በዓሉ በመስቀል አደባባይ እና በምንሊክ አደባበይ የተከበረ ሲሆን ታቦቶችም ወጥተው ነበር። በዚህ ዓመት የተከበረው የመታሰቢያ በዓል ለመጀመሪያ ግዜ በሕዝብ ፍላጎትና ተነሳሽነት የተከበረ እንደሆነም ይነገርለታል። ባጠቃላይ ግን 21 ግዜ መድፍ መተኮስ የአበባ ጉንጉን ማስቀመጥ፤ በማርሽ ባንድ መታጀብ እና የአርበኞች ሽለላ ሳይቆራረጡ ቀጥለዋል። ዘንድሮም የጎደለውን ሞልተን የተሳሰሳተውን አርመን ሕግና ስርዓትን በጠበቀ መልኩ ከመሰዳደብ እና ከመተቻቸት ወጥተን ያባቶቻችንን የነጻነት ገድል እኛም የነሱ ልጆች መሆናችንን በሚመጥን ደረጃ ማክበር ይጠበቅብናል፤ መልዕክቴ ነው።

# ‹‹የዓድዋ ድል በአህጉር ደረጃም የድል ቀን ተደርጎ ሊከበር የሚገባው ታላቅ የታሪክ እጥፋት ነው››

ሰማኸኝ ጋሻው
የታሪክ መምህርና ተመራማሪ

አስቴር ኤሊያስ

**የዓድዋ ድል በየዓመቱ ሲከበር ሁሌም ለኢትዮጵያ የአሸናፊነትና የደስታ፤ ለጣሊያን ደግሞ የተሸናፊነትና የሀዘን ጊዜን የሚያስታውስ ነው። በኢትዮጵያውያኑና በመላ ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ የዓድዋ ድል የሚንቦገቦግ የነጻነት ቀንዲል ሲሆን፣ ለጨቋኞችና ለቅኝ ገዢዎች ግን የመሸነፍን መራር ጽዋ የተጎነጨበት ዘመንን የሚያስታውስ እንደመሆኑ ቁጭትንና አግራሞትን የሚያጭር ነው፡፡**

**እንደሚታወቀው የጥቁር ሕዝቦች ድል የሆነው ዓድዋ፣ ዘንድሮ ለ128ኛ ጊዜ ከነገ በስቲያ በተለያዩ መርሃግብር የሚከበር ይሆናል። ይህን ታላቅ ድልን አስመልክቶ አዲስ ዘመን ዓድዋ ላይ የነበረው የአንድነት መንፈስ ዛሬ ላይ ለምን ሲደበዝዝ ቻለ በሚሉና ሌሎችም ተያያዥ ጥያቄዎችን በማንሳት በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር እና ተመራማሪ ከሆኑት ሰማኸኝ ጋሻው ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል። መልካም ንባብ፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- የዓድዋ ድልን እንደምን ይገልጻሉ?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** ዓድዋ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ የታሪክ እጥፋቶች መካከል አንዱ ነው ብንል ማጋነን አይደለም። የሰው ልጅን የእርስበእርስ ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት መልክ ካስያዙ ክስተቶች መካከል ምናልባት የታላላቅ ሃይማኖታዊ አስተምርሆዎች መነሳት በዋናነት ሊጠቀስ ይችላል። ምክንያቱም ሃይማኖቶቹ በአስተምርሆዎቻቸው የሰው ልጆችን እኩልነት በመርህ ደረጃ ማስተማር መቻላቸው ነው።

የሰው ልጅ እንደሚኖርበት አካባቢና ከወላጆቹ እንደሚወርሰው ዘመን የተለያየ ባህል፣ ወግ እና ልምድ እንዲሁም ቀለም፣ ቅርፅና ቁመና ይኖረዋል። ይህ ነባራዊ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ በተቃራኒ የሰው ልጅ እራሱን “ነጭ፣ ቀይና ጥቁር” በሚል ዘረኛ አስተሳሰብ ይመድባል። በሂደት እሳቤው የሰው ዘርን “ታላቅ” እና “ታናሽ” ብሎ ወደ መከፈል ደረጃ አደገ። ይህ የተዛባ አስተሳሰብ ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም፣ በ19 እና 20ኛው ምዕት ዓመት ላይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። እዚህ ላይ አውሮፓ ወለድ የሆኑት የጆርጅ ሄግል እና የቻርለስ ዳርዊንን ዘረኛ አስተሳሰቦችን ማስታወስ በቂ ይሆናል። ሁለቱ የወቅቱ ልሂቃን “ነጭ” የተባለውን “ዘር” የተሻለ የሰው ዘርና የተሻለ ባሕል ባለቤት እንደሆነ ይስማማሉ። ይህ እሳቤ እየዳበረ በመሄዱ “ጥቁር” የሰው ዘር ለባርነት ብቻ የተፈጠረ እስኪመስል ድረስ በ19ኛው ምዕት ዓመት በባርነት አጋዙት። እዚህ ላይ በታሪክ “የአትላንቲክ የባሪያ ንግድ (Atlantic Slave Trade)” የሚባለውን ክስተት ማስታወስ በቂ ነው።

በአትላንቲክ የባሪያ ንግድ ምክንያት አፍሪካውያን ጉልበታቸው ብቻ ሳይሆን እውቀታቸውም ወደ አውሮፓ ተሰደደ። ይህ ክስተት በአውሮፓ የሀብት ክምችት (Capital accumulation) እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ (Technological Enovation) እንዲከሰት አደረገ። ስለዚህ በአፍሪካውያን ባሮች የተገነባው ካፒታሊዝም በሂደት የኢንዱስትሪ አብዮትን ወለደ። በአውሮፓ የኢንዱስትሪ መስፋፋትን ተከትሎ፤ ለፋብሪካዎች ግብአት የሚሆን ጥሬ እቃ እና የሸቀጥ ማራገፊያ ቦታ አስፈለገ። አውሮፓውያን ይህንን ፍላጎታቸውን ለማሳካት ወደ ኢምፔሪያሊዝም (Living on the cost of other) ደረጃ አሳደጉ።

በዚህ ፅንሰ ሀሳብ ከተስማሙ በኋላ አፍሪካውያንን በቅኝ ግዛት ለመቀራመት ህጋዊ መሰረት ማስያዝ ስለነበረባቸው በጀርመኑ መሪ ኦቶማን ቢስማርክ መሪነት እ.ኤ.አ በ 1884 “የበርሊን ኮንፈረስን” በበርሊን ከተማ አካሄዱ። በዚህ ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት እንድትሆን ተወሰነላት።

በእርግጥ ኢጣሊያ ቀደም ብላ እ.ኤ.አ በ1885 በእንግሊዝ አጋዥነት የምፅዋ ወደብን ተቆጣጥራ ነበር። እንዲሁም እ.ኤ.አ በ1882 የአሰብ ወደብን “ሮባቲኒዮ” ከሚባል የጣሊያን የግል መርከብ ኩባንያ ተረክባ ነበር። እነዚህን ሁለት ወደቦች ቀድማ መቆጣጠር በመቻልዋ፤ በበርሊን ጉባዔ ያቀረበችው ጥያቄ በቀላሉ ተቀባይነት አገኘ። “ሮባቲኒዮ” የተባለው የግል ኩባንያ በበኩሉ፤ እ.ኤ.አ በ1896 በወቅቱ የአፋር ገዢ ከነበረው ሱልጣን ራሂታ በስድስት ሺ ጠገራ ብር የአሰብ ወደብን ገዝቶ ነበር። እነዚህ እንቅስቃሴዎቿ ለቀጣይ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት ላቀደችው እቅድ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ቻለ።

እንግዲህ የዓድዋ ጦርነት ማለት በቅኝ ገዥዎች እና ተገዥዎች፣ በወራሪዎችና ተወራሪዎች፣ በነጮችና ጥቁሮች፣ በበዝባዦችና ተበዝባዦች፣ በጨቋኝና ተጨቋኞች፣ በዘረኞችና ፍትህ ናፋቂዎች፣ በሰው ልጆች እኩልነት በሚያምኑና በማያምኑ የሰው ልጆች መካከል የተካሄደ ፍትሃዊ ጦርነት ነው። እኔን እስከገባኝ ድረስ የሰው ልጆችን እኩልነት ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጦርነቶችን “ቅዱስ” ጦርነቶች ብለን ብንሰይማቸው የሚጎድላቸው ነገር የሚኖር አይመስለኝም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከሰሞኑ የኢፌዴሪ መንግስት በዚህ “ቅዱስ” ጦርነት ለተሳተፉ የዓድዋ ጀግኖች የመታሰቢያ ሙዚየም ማስመረቁን አይተናል።

ጉዳዩን በአስተውሎት ለተመለከተው ሰው በዚህ ፍትሃዊ ጦርነት መስዋዕትነት ለከፈሉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የመታሰቢያ ሙዚየም መሰራቱ እጅግ ይበል የሚያስብል ተግባር ነው። አስቀድሜ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ይህ ድል ለሁሉም ጥቁር ሕዝቦች እኩልነት የተከፈለ የደም ዋጋ ነው። ይህ ታላቅ የሆነው የዓድዋ ድል በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በመላ የአፍሪካ አገሮች እንደ አህጉራዊ የድል ቀን ተደርጎ ሊከበር የሚገባው ታላቅ የታሪክ እጥፋት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። በተጨማሪም የዓድዋ ድል በሰው ልጆች ነፃነትና እኩልነት የሚያምን ማንኛውም የሰው ዘር ሊያከብረውና ሊዘክረው የሚገባ ክስተት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን የተመረቀውን የዓድዋ —ዜሮ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም“ እንደ አንድ የታሪክ ምሁር እንዴት አዩት? ፋይዳው ምንድን ነው ይላሉ?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** ይህን ታሪካዊ ጀብዱ ለፈፀሙ ጀግኖቻችን፣ መታሰቢያ ሙዚየም መገንባት መቻሉ ታሪካዊ ጠቀሜታዎች አሉት። የመጀመሪያው ጠቀሜታ ታሪክን ጠብቆ ለተተኪ ትውልድ ለማስተላለፍ ማስቻሉ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ መሆኑ ሲሆን፣ የቱሪዝም ሴክተሩን ማነቃቃት ያስችላል። ሶስተኛው የታሪክ ስበት ማዕከሉን አገራችን ኢትዮጵያ ላይ እንዲቆይ ያስችላል። ኢትዮጵያ ታሪካዊት አገር፤ ሕዝቧም የዚህ ታላቅ ጀብዱ ባለቤት እንዲሁም የነፃነት፣ የጀግንነት ተምሳሌ ሆና እንድትቀጥል ያስችላታል። አራተኛው ደግሞ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው የእርስ በእርስ እና ወንድማማችነት መንፈስ የበለጠ እንዲጠናከር ያደርጋል።

እንደሚታወቀው ዓድዋ በዋናነት የመላ ኢትዮጵያውያን የጋራ ድል ነው። ከሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ከባዱን የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለውበታል። በዚህ ድል ለተሰው ጀግኖች የመታሰቢያ ሙዚየም ተሰራላቸው ማለት፤ በድሉ ላይ ያላቸው የባለቤትነት ስሜት እንዲጨምር ያደርጋል። ይህ ደግሞ አብሮነትን ያጠናክራል። አምስተኛው ደግሞ የብሔረ መንግስት ግንባታውን ሂደት ያፋጥነዋል። የብሔረ መንግስት ግንባታ ማለት በአንድ ሉአላዊት አገር ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች በዋና ዋና አገራዊ ምልክቶች ላይ የጋራ ግንዛቤና የባለቤትነት ስሜት መፍጠር መቻል ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ እንደምናውቀው የአገረ መንግስት ግንባታው ቀደም ብሎ የተከናወነ ቢሆንም ቅሉ የብሔረ መንግስት ግንባታው ግን የተቋጨ ጉዳይ አይመስለኝም። በአጠቃላይ የጀግኖቻችን መታሰቢያ ሙዚየም መሰራቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

> **የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካን ለአንድ ምዕት ዓመት ያክል በዝብዘዋል። ነገር ግን ኢትዮጵያ የተቃጣባትን ወረራ በተሳካ መልኩ ዓድዋ ላይ እ..ኤ.አ ከ1896 መክታ መልሳለች**

**አዲስ ዘመን፡- የአድዋ ድል ከኢትዮጵያ አልፎ የመላ ጥቁር ሕዝቦች እና የጭቁኖች የነጻነት ምልክት ነው የሚባለው እንዴት ነው?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** ከአድዋ ጦርነት በፊት በነጮችና ጥቁሮች መካከል የነበረው ተፈጥሯዊ ግንኙነት የተዛባ ነበር። ነጮቹ ራሳቸውን እንደ ገዢ ሲቆጥሩ፣ ጥቁሮቹን ደግሞ እንደ ተገዢ ሕዝብ ይቆጥሩት ነበር። ጥቁሮቹ ራሳቸውን የማስተዳደር አቅምና ችሎታ እንደሌላቸው ይቆጥሩ ነበር። በተጨማሪም ጥቁሮች ባህልና ታሪክ አልባ፤ እንዲሁም በተፈጥሯቸው ያልተሟሉ የሰው ዘሮች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገር ነበር።

በዚህም ምክንያት ነጮቹ ወደ አፍሪካ አኅጉር በመጡ ወቅት፤ “እኛ ጥቁሮችን ለማስተዳደርና ለማሰልጠን ከአምላክ የተላክን ነን፤ ጥቁሮች የሚኖሩበትን ጨለማ አህጉር ለማሰልጠን መጥተናል” በማለት ሕዝቡን ያደናግሩ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም የማጭበርበሪያ ስምምነቶችን ከአፍሪካ መሪዎች ጋር በመፈራረም አፍሪካን በቅኝ ግዛት ስር ማስገባት ጀመሩ።

እዚህ ላይ ለዓድዋ ጦርነት መከሰት መንስዔ የሆነውን የውጫሌ ሰምምነትን ማስታወስ ግድ ይላል። ይህ ውል በዳግማዊ ምኒልክና በጣሊያን መንግስት ወኪል አንቶሎኒ መካከል የተፈረመ ሲሆን፣ አንቀፅ 17 የያዘው አወዛጋቢ ትርጉም ለጦርነቱ መከሰት የቅርብ መንስኤ ሆኗል። የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በዚህ መልኩ እ.ኤ.አ ከ1870ዎቹ እስከ 1960ዎቹ ከኢትዮጵያ በስተቀር በቅኝ ግዛት ስር አደረጉ።

የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካን ለአንድ ምዕት ዓመት ያክል በዝብዘዋል። ነገር ግን ኢትዮጵያ የተቃጣባትን ወረራ በተሳካ መልኩ ዓድዋ ላይ እ..ኤ.አ ከ1896 መክታ መልሳለች። በወቅቱ ነጭ እንደ አውራ ዘር (Master race) በሚቆጠርበት ወቅት አሸንፎ ለሌሎች አገሮችና ሕዝቦች አርዓያ መሆን መቻል ታላቅነት ነው። ይህንን የተዛባ ታላቅ ትርክት መስበር የቻለች ብቸኛዋ አገር ኢትዮጵያ ናት፤ ጥቁሮች ነጮችን ማሸነፍ እንደሚችሉ ቀድማ ያበሰረች አገር ናት።

ከዓድዋ ድል ማግስት በርካታ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ቀንበር ለመላቀቅ የነፃነት ትግላቸውን አጠናክረው

**ወደ ገጽ 8 ዞሯል**

# ወቅታዊ

# ‹‹የዓድዋ ድል በአህጉር ደረጃም የድል ቀን...

ከገጽ 7 የዞረ

ቀጠሉ። ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ በ1900ዎቹ በታንጋኒካ የተከሰተው የማጅ ማጅ እንቅስቃሴ፤ በ1940ዎቹ በኬንያ የተከሰተው የማው ማው እንቅስቃሴ እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ የተከሰተው የኢትዮጵያኒዝም እንቅስቃሴዎች ታላቅ ማሳያዎች ናቸው። በተጨማሪም ወደ 16 የሚደርሱ የአፍሪካ አገሮች የነፃነት ምልክት የሆነችዋን የኢትዮጵያን ባንዲራ በተለያየ ዲዛይን ለአገራቸው ምልክትነት ተጠቅመዋል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ዓድዋ ላይ ያስመዘገበችው ድል ለሌሎች አፍሪካውያን አገሮች ትልቅ የነፃነት በር የከፈተ ማርሽ ቀያሪ ክስተት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙዎቹ እንደሚሉት፤ የዓድዋ ድል ነጮችን ያስደነገጠ ድል ነው፤ ይህን እርስዎ እንዴት ይገልጹታል?**

**መምህር ሰማኸኝ፤-** እንደሚታወቀው የዓድዋ ድል ታላቅ የታሪክ እጥፋት ያስከተለ ክስተት ነው የምንለው በሁለቱም ማለትም በነጮችና በጥቁር ሰው ልጆች ዘንድ ያሳደረውን ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በአውሮፓውያን ነጮች ዘንድ ታላቅ ድንጋጤና ስጋት የፈጠረ ክስተት ሲሆን፣ በአፍሪካውያን ጥቁሮች ዘንድ ደግሞ ታላቅ ደስታና ሃሴትን መፍጠር የቻለ ክስተት ነበር። በአውሮፓውያን በኩል፣ ነጮች ይከተሉት የነበረው የተዛባ ትርክት "የነጭ ዘር የበላይነት" መንኮታኮትና እርቃኑን መቅረት የጀመረው በዓድዋ ድል ምክንያት ነው። ከዚህ ድል በኋላ ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካ ላይ የነበራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጥቅሞች መናጋት ጀመሩ። ከኢኮኖሚያዊ ስጋቶች መካከል አፍሪካን ቅኝ በመግዛት፣ ለኢንዱስትሪዎቻቸው ያካበቱት የነበረው የጥሬ ሀብት ሊቋረጥ እንደሚችል የተገነዘቡበት ክስተት ተፈጠረ። ምክንያቱም አፍሪካውያን ነጮችን ማሸነፍ እንደሚችሉ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ መማር ችለዋል። ጥሬ ሀብት የሚዘርፉበት ቦታ ብቻ ሳይሆን የኢንዱስትሪ ሸቀጦቻቸውን የሚያራግፉበት ቅኝ ተገዥ አገሮችን ማጣት እንደሚችሉ የተገነዘቡበት ጭምር ክስተት ነው።

በፖለቲካው ዘርፍ ስንመለከት ደግሞ፤ በወቅቱ በአውሮፓውያን ዘንድ ቅኝ ግዛት መያዝ እንደ ክብር መገለጫ ይቆጠር ነበር። በዚህም ኃያልነታቸውን ለማሳየት ከአፍሪካ አገሮች ውስጥ በወረራ መያዝ እንደ ጀብዱ ይቆጥሩታል። እንዲያውም ክብራቸውን ለማሳየት ሲሉ አንዳንዴ የእርስበርስ ፉክክር ውስጥ ሁሉ ይገቡ ነበር። ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ እንግሊዝና ፈረንሳይ ሱዳንን ለመቆጣጠር ፉክክር ውስጥ ገብተው ነበር።

ባሕላዊ ዘርፉን በተመለከተ ቅኝ ገዥዎች የአፍሪካውያንን ባሕልና ወግ በመደፍጠጥ የነርሱን ጭነውባቸው ነበር። በዚህም አፍሪካውያን ማንነታቸውን፤ ታሪካቸውን ተነጥቀው ማንነት አልባ ሆነው ነበር። ይህ ትክክል እንዳልነበር የተረዱት ከዓድዋ ድል ማግስት ጀምሮ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ለጥቁር አፍሪካውያን እና በሰው ልጆች እኩልነት ለሚያምን የሰው ዘር ሁሉ መልካም ብስራት የተሰማው በዓድዋ ታላቅ ድል ምክንያት ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በዓድዋ ድል የሰው ልጆችን እኩልነት ማረጋገጥ እንደቻለች ይነገራል፤ በባርነት ቀንበር ውስጥ የነበሩ ሕዝቦችም የዓድዋ ድል አርዓያ እንደሆናቸው ይታወቃልና ይህ ታላቅ ድል የተገባውን ያህል በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተነገሮለታል ይላሉ?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** ዓድዋ ለሰው ልጆች በተለይም ደግሞ ለአፍሪካውያን ያስገኘውን ጠቀሜታ ያህል ተዘክሯል ብዬ አላምንም። እንዲሁም ለድሉ ግንባር ቀደም ባለቤት የሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ እራሱ የሚጠበቅባትን ያህል ትኩረት አልሰጠችም ነበር። ዛሬ ላይ የዓድዋን 128ኛ ዓመት እያከበርን ብንሆንም ቅሉ ይህን ሁሉ ዓመታት ዓድዋ በስሙ የሚጠራ አንድም ብሔራዊ ተቋም አልነበረውም። ታሪክ የተሰራባቸው የዓድዋ ተራሮች ዛሬም ምንም አይነት መሰረተ ልማት የላቸውም፤ ለጥናትና ምርምር፤ ለቱሪስት መስዕብ ሊውሉ የሚችሉ ተቋማት ዛሬም አይስተዋሉም።

በተመሳሳይ አፍሪካውያን ድሉ የጋራቸው መሆኑን ተገንዝበው ታሪኩን የሚመጥን ስራ ሲሰሩ አይስተዋሉም። ዛሬም ድረስ ለዓድዋ መታሰቢያ ሊሆኑ የሚችሉ የጥናት ማዕከሎች በአፍሪካ አገሮች አይስተዋሉም። ይህ የራስን



ታሪክ ከማቃለል፤ የተከፈለውን መስዋዕትነት ካለመረዳት እንዲሁም ታሪካዊ ፋይዳውን በአግባቡ ካለማወቅ የሚመነጭ ይመስለኛል።

በእርግጥ ከቅኝ ግዛት ዘመን በኋላ በአፍሪካ የተመሰረቱ መንግስታት ከአዲሱ ቅኝ ግዛት አስተሳሰብ (Neocolonialism sentiments) ነፃ የወጡ ናቸው ብዬ አላምንም። አሁንም ድረስ በድሮ ቅኝ ገዥዎቻቸው ተጽዕኖ ስር በመሆናቸው ለዓድዋ የሚሰጡት ትኩረት እጅግ ያነሰ እንዲሆን አድርጎታል።

በታሪካዊ የጥናት ዘርፉም ቢሆን ዓድዋ የድሉን ግዝፈት ያህል ተጠንቷል ብዬ አላስብም። ለምሳሌ በዓድዋ ጦርነት ላይ ስነህይወታዊ ጦርነት (Biological war) በኢትዮጵያ ላይ ተፈፅሟል ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ፋሽስት ኢጣሊያ "አባ ሰንጋ" በተባለ የከብት በሽታ የተጠቃ ከብት በምፅዋ ወደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ከፍተኛ ጉዳት አድርሳለች። በዚህ የተነሳ በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ በታሪክ "ክፉ ቀን" የተባለው ዘመን እ.ኤ.አ ከ1889 እስከ 1892 ተከስቶ ነበር። ይህ ክስተት ኢትዮጵያውያንን ክፉኛ ከመጉዳቱም በላይ ኢጣሊያ አገራችንን ለመውረር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር አስባ የፈፀመችው እኩይ ሴራ ይመስለኛል። ነገር ግን እስካሁን በጥናት ተደግፎ ሊቀርብ አልቻለም።

**አዲስ ዘመን፡- ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን አንድነት ትልቅ መሰረት የሆነና ጥልቅ ትርጉም ያለው ነው፤ ዛሬስ ልክ እንደ ዓድዋው ጊዜ ያንን የሚመስል አንድነት አለ? የዓድዋን ድል ለከፍታችን መነሻነት የማንጠቀመው ለምንድን ነው?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** ኢትዮጵያውያንን አንድ ከሚያደርጉን ታሪካዊ ክስተቶች ውስጥ ዓድዋ የአምበሳውን ድርሻ ይወስዳል። ነገር ግን የዓድዋ ዘመን ትውልድ የአንድነት መንፈስ በዛሬው ትውልድ ላይ ጎልቶ አይታይም፤ ይህ ደግሞ የራሱ መሰረታዊ ምክንያቶች አሉት። በእርግጥ የዛሬው ትውልድም በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የማያወላዳ አቋም እንዳለው በተለያዩ ሀገራዊ ጥሪዎች ላይ በተግባር አሳይቷል። በቅርቡ እንኳ በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ አሰጣጥ ላይ አንድነቱን አሳይቷል። ሆኖም ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙም ያልተለመዱ፤ ለአብሮነታችን እንቅፋት የሚሆኑ ድርጊቶች ሲከሰቱ ይስተዋላሉ።

ዓድዋ የጋራ አምድ እንደመሆኑ መጠን እንደ ዓድዋ ጀግኖች አባቶቻችን የአንድነት ማሰሪያ ፅኑ ቃልኪዳን ልናደርገው ይገባ ነበር። ነገር ግን በፊት ለፊት ጦርነት ዓድዋ ላይ የተሸነፉት ኢምፔሪያሊስቶች ስልታቸውን በመቀየር ሊያግባባን በማይችል የፖለቲካ ሪዕዮትዓለም ውስጥ ከተቱን። በሽንፈታቸው ጥርስ የነከሱት አውሮፓውያን፤ ኢትዮጵያን በምን መልኩ ማፍረስ እንደሚችሉ ዘዴ ከመፈለግ አላረፉም ነበር። ለምሳሌ ባሮን ፕሮቻዝካ የተባለው ፀሀፊ "Abyssinia: The Powder of Barrel" በተሰኘውና በእ.ኤ.አ በ1935 ባሳተመው መፅሀፉ ኢትዮጵያውያን አንድ እንዳይሆኑ አዳዲስ የሀሰት ትርክቶችን ጠቅሷል።

ከነዚህ መካከል የ"ብሔር" ጭቆና እንደነበር፤ አገሪቱም ቅኝ መገዛት እንዳለባት፤ ነባር ተቋማት በጠላትነት እንዲፈረጁ አቅጣጫ ሰጥቷል። እንዳለመታደል ሆኖ የ1960ዎች ትውልድ ይህንን የተዛባ ትርክት የሀገሪቱ ፖለቲካዊ ማዕዘን አድርጎ አስቀጠለው ይህ ዛሬ ያለንበትን ፖለቲካዊ ስብራት ፈጠረ።

በመሆኑም እኛ ኢትዮጵያውያን ጦር መዝዞ የመጣውን ኃይል ቀደም ብሎ ዶጋሊ ላይ በመቀጠል ደግሞ ዓድዋ ላይ ፊት ለፊት ተጋፍጠን ማሸነፍ ቻልን እንጂ፤ መልኩን ቀይሮ በኛ ሰዎች በኩል የመጣውን የቅኝ ገዥዎች ድብቅ ሴራ ማሸነፍ አልቻልንም። ይህ ደግሞ የዛሬው ትውልድ እንደ ዓድዋ ትውልድ በተሟላ መልኩ በአንድነት እንዳይቆም እንቅፋት የፈጠረበት ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያውያን የዓድዋ ልጆች መሆን ያቀተንስ ለምንድን ነው? የዓድዋ ልጆች መሆን እንድንችል ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** የዛሬው ትውልድ እንደ ዓድዋ አባቶች መሆን ያልቻለው በአስተሳሰብ ጦርነቱን መሸነፉ ነው። የግንባር ጦርነቱን በድል ከተወጣ በኋላ ፖለቲካዊ አይዶሎጂካል ጦርነቱን ግን ተሸንፏል። ትውልዱ የራሱ የሆነ አገር በቀል ፖለቲካዊ ተቋማትን ከመገንባትና ከማጠናከር ይልቅ በዴሞክራሲ ሽፋን የተመረዘ 'አብዮታዊ" ዴሞክራሲን ተከለ። ይህ መልካም የሚመስል ግን ደግሞ አደገኛ የሆነው እሳቤ ተቋማዊ ቅርፅ በመያዝ መሰረታዊ የአብሮነትን መርህ ማናጋት ቻለ።

ወደ አባቶቻችን የአብሮነት ስሜት ለመመለስ ከተፈለገ መነጋገር፤ መወያየትና መደማመጥ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሁሉም ሰው ከስሜትና ሆደ ባሻነት መላቀቅ አለበት። መንግስትም ሕዝብ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች በሰከነ መልኩ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ግዴታው ነው ብየ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ዓድዋ ልጆች የማንሆን ከሆነ የሚያጋጥመን ምንድን ነው? መፍትሔውስ?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** እንግዲህ ታሪክን የምንመረምር ካለፈው ድርጊታችን ትምህርት ለመቅሰም ነው። ሰዎች በግለሰብም ይሁን በማኅብረሰብ ደረጃ የታሪካዊ ክስተቶች ድምር ውጤት ናቸው። አገርም እንዲሁ የታሪኳ ድምር ውጤት ናት። እንደ አገር ካለፉ ድርጊቶቻችን ትምህርት የማንወስድ ከሆነ፤ የከፋ አደጋ ሊገጥመን ይችላል። በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፎ ያውቃል፤ ዛሬ የገጠመውንም ከዓድዋ ጀግኖች በወረሰው ጥበብ ይሻገረዋል ብዬ አምናለሁ።

በመሰረቱ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ተጋጭቶ አያውቅም። መሪዎቹ ግን በተለያዩ የውጭና የውስጥ ግፊቶች ምክንያት ሽኩቻ ውስጥ ይገባሉ። በዓድዋ ጦርነት ወቅት፤ ጣሊያን ትከተለው በነበረው የማግባባት ፖሊሲ ምክንያት በትግራይና "መረብ ምላሽ" አካባቢ የነበሩ ገዢዎች ጣሊያንን ሊተባበሩ ሞክረው የነበረ ቢሆንም፤ የጣሊያንን መሰሪ አካሄድ በመገንዘብ ከወቅቱ ንጉሰ ነገስት ዳግማዊ ምኒልክ ጋር ታርቀው ጠላትን በጋራ ተጋፍጠው ድልን አውርሰውናል።

ዛሬም ቢሆን ሕዝብ እንደ ሕዝብ አልተጋጨም። የችግሩ ምንጭ ዓድዋ ላይ ያሸነፍናቸውን ቅኝ ገዥዎችን ስነ ልቦና ከወረሱት ጥቁር ኮሎኒያሊስት "ምሁራን" ነው። እነርሱም የፖለቲካ ስብራታችን ውጤቶች ይመስሉኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ዓድዋንና ፓን አፍሪካኒዝምን የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው?**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** የዓድዋና የፓን አፍሪካኒዝም ግንኙነትን ስንመለከት በቅደም ተከትል የተከሰቱ ተመሳሳይ ዓላማ የነበራቸው ታሪካዊ ክስተቶች ናቸው። ዓድዋ ቀደም ብሎ የኢምፔሪያሊስቶችን እኩይ ዓላማ ለመመከት እ.ኤ.አ በ1896 የተከሰተ ሲሆን፤ ፓን አፍሪካኒዝም ደግሞ የዓድዋን ተሞክሮ በመቅሰም እ.ኤ.አ ከ1900ዎቹ ጀምሮ መላ ጥቁር አፍሪካውያንን ከቅኝ ግዛት ቀንበር ለማላቀቅ መነሻውን በአሜሪካ ካሪቢያን አገሮች አድርጎ ለመላ ጥቁር ሕዝብ ነፃነት የታገለ ድርጅት ነበር።

የዚህ እንቅስቃሴ ጠንሳሾች በሕንድና አሜሪካ ይኖሩ የነበሩ የጥቁር ሕዝብ ዘሮች ነበሩ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ማርከስ ጋርቬ እና ዱ ቦይስ የተባሉ አፍሮ አሜሪካውያን ይገኙበታል። በተጨማሪም ከአፍሪካ አህጉር ውስጥ ዋና ዋና የፓን ቀደምት አፍሪካኒዝም አቀንቃኞች፤ ዶክተር ዊልሞት ባይደን እና ቢሾፕ ጆህንሰን ከምዕራብ አፍሪካ ይገኙበት ነበር። ቢሾፕ ጆህንሰን፤ ነጮች ክርስትናን በአፍሪካ ለማስፋፋት በሚል ስም የጥቁሮችን ተፈጥሮዊ መብት ምን ያህል እንደሚጥሱ ስለተገነዘበ፤ በጥቁር ሃይማኖታዊ አባቶች የምትመራ ቤተክርስቲያን ለማቋቋም ጥረት ያደርግ ነበር።

ፓን አፍሪካኒዝምን /ፓን ብላክ/ ማለት ሁሉም አፍሪካውያን /ሁሉም ጥቁር ሕዝብ/ እንደማለት ሲሆን፣ ከቅኝ ገዥዎች /ነጮች/ ጭቆና ነፃ ለመሆን የሚደረግ የትግል እንቅስቃሴን ያመለክታል። ፓን አፍሪካኒዝምን በትግሉ ውስጥ በመላው ዓለም የነበሩ ጥቁሮች ሁሉ በንቃት እንዲሳተፉ ያመቻቸ ተቋም ነበር።

**ይህ** እንቅስቃሴ ከ1900ዎቹ ጀምሮ በአሜሪካና በአውሮፓ የተለያዩ መድረኮችን ሲያካሂድ ከቆየ በኋላ፤ ከአፍሪካ ወጣት ፖለቲከኞችን በማካተት የነፃነት ትግሉን አፋጥኗል። ከእነዚህ ውስጥ የወቅቱ የናይጄሪያው መሪ ናምዲ አዚኪው፤ የጋናው መሪ ኩዋሜ ንኩርማህ፤ የኬንያው መሪ ጆሞ ኬኒያታ፣ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴን በማካተት የአፍሪካ ሕብረት ድርጅትን ወለደ። የአፍሪክ ሕብረት ምስረታ ፅንሰ ሃሳብ እ.ኤ.አ በ1945 በማንችስተር ከተማ በተካሄደው ጉባዔ ላይ ተቀባይነት አገኘ። በሂደትም የአፍሪካ ነፃ አገሮች በአንድ መዋቅራዊ ጥላ ስር ተካተው የፀረ ቅኝ ግዛት ትግሉን ማፋጠን ቻሉ።

በአጠቃላይ ሲታይ፤ የዓድዋ ድል ለፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ መነሻ እንዲሁም ለአፍሪካ ሕብረትና በኋላም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ታሪካዊ ክስተት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**መምህር ሰማኸኝ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን በዘላቂነት የማሳደግ ጥረት

**አንተነህ ቸሬ**

በምጣኔ ሀብታቸውና በፖለቲካ ተፅዕኗቸው የዓለም ኃያላን የሆኑት ሀገራት ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ በርካታ ተግባራትን ያከናውናሉ። እነዚህ ሀገራት ባለሀብቶቻቸውን በማገዝና በመጠበቅ እረገድ የሰሩት ስራ የአምራችነት አቅማቸውን አሳድጎ የምጣኔ ሀብት እድገታቸው ዘላቂ እንዲሆን አስችሎታል። ለማይናወጥ ምጣኔ ሀብትና ለኃያልነታቸው መሰረት የሆነው ከውጭ ጥገኛነት በመላቀቅ የማምረት አቅም ማሳደግ መቻላቸው እንደሆነ ይታወቃል። እነዚህ ሀገራት አሁንም ቢሆን ባለሃብቶቻቸውን የሚያበረታቱባቸው ልዩ የድጋፍና ጥበቃ መርሃ ግብር አላቸው። የምጣኔ ሀብት ጥናቶች እንደሚያስረዱት፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለዘላቂ የሀገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉ የልማት አንቀሳቃሾች ናቸው።

ኢትዮጵያውያን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎና ድርሻ በየጊዜው እየተሻሻለ እንደመጣ ባይካድም በቂ የሚባል ግን አይደለም። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሚታየው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፎና ድርሻ ተስፋ ሰጭ ሆኗል።

የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መደረጉ፣ ለኢንቨስትመንት እድገት መሰናክል የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች መሻሻላቸው፤ በመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ በአገልግሎት አሰጣጥና ተያያዥ ዘርፎች እየተገበረ ያለው ቀልጣፋና ፈጣን አሰራር፤ የኢንቨስትመንት ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ስራዎች፤ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲገቡ በመንግሥት ልዩ አቅጣጫ መቀመጡና ትኩረት መሰጠቱ እና የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ያለሙ የሪፎርም ስራዎች መተግበራቸው ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፎና ድርሻ ማደግ ምክንያቶች ሆነው ይጠቀሳሉ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች በማምረቻው ዘርፍ የነበራቸው ተሳትፎ አበረታች እንደሆነ ሰሞኑን የመስሪያ ቤታቸውን የስድስት ወራት የስራ አፈፃፀም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረቡበት ወቅት ገልፀዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ 30 ቢሊዮን ብር ካፒታል የሚያስመዘግቡ 301 የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን በአምራች ዘርፉ ለማሰማራት ታቅዶ፣ ከ29 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ 292 ባለሃብቶች አምራች ዘርፉን እንዲቀላቀሉ ማድረግ ተችሏል። በግማሽ ዓመት በአምራች ኢንዱስትሪው ከተፈጠረው 120ሺ 793 የስራ እድል መካከል 105ሺ 910 የሚሆነው የስራ እድል የተፈጠረው በሀገር ውስጥ ባለሃብቶች አማካኝነት ነው።

በምግብና መጠጥ ዘርፍ (በዱቄት፣ በዳቦ፣ በምግብ ዘይት፣ በፓስታና ሞኮሮኒ፣ በውሃ፣ በጁስ፣ በብርዕና አገዳ እህሎች ማቀነባበር፣ በቡና ማቀነባበር፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበር እና በለስላሳ መጠጥ ምርት) 104፣ በኬሚካልና ኮንስትራክሽን (የወረቀትና ካርቶን እና፣ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻ) 94፣ በማኑፋክቸሪንግ ኢንጂነሪንግ (ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስ፣ አውቶሞቲቭ እና ማሽነሪ ምርት) 80፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት 12 እንዲሁም በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ሁለት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ ስራ ገብተዋል።

አቶ መላኩ የፀጥታ ችግሮች፣ የመስሪያ ቦታዎች በበቂ ሁኔታ አለመዘጋጀት እና በአዲስ አወቃቀር ምክንያት የአንዳንድ ክልሎች ፈጥነው ወደ ስራ አለመግባት አዳዲስ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም መሰናክል መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ለእነዚህ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች አቅም ማደግ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉትን የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ልማት ስራዎችን በትኩረት መስራት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ፣ በ2016 ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከገቡ አምራቾች መካከል ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እንደሆኑ ይገልፃሉ። እንደ አቶ አክሊሉ ማብራሪያ፣ ባለፈው አንድ ዓመት በልዩ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን የማነቃቃት፣ የማበረታታትና ወደ አምራች ዘርፉ ገብቶ ውጤታማ ስራዎችን እንዲሰራ የማድረግ ስራ ነው። በዚህ ሂደት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ አምራች ዘርፉ እንዳይገቡ መሰናክል የነበሩ ችግሮች ተለይተው መፍትሄ እያገኙ ነው።

> **ኢትዮጵያ በስራ አጥነትና በዋጋ ንረት እየተፈተነች ባለችበት በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው። የመንግሥት ድጋፍ ምጣኔ ሀብቱን በማነቃቃት፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የገቢ ንግድ እቃዎችን በመተካት፣ የወጪ ንግድን በማሳደግ ጥቅል ሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንዲኖረው ያደርጋል**

ዋና ስራ አስፈፃሚው እንዳሉት፣ ከዚህ ቀደም ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች የሚሰጠው ቦታ አነስተኛ ነበር። በ2015 እና 2016 ዓ.ም የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እንዲነቃቁ ባለሃብቶቹ ያሉባቸውን የፋይናንስና ሌሎች ክፍተቶችን የሚሞሉ ተግባራት ተከናውነዋል። በመሆኑም በ2015 እና ዘንድሮ ከተመዘገቡት ባለሃብቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው። አንዳንድ ችግሮች ሲፈጠሩ ጓዙን ጠቅልሎ የሚሄድ የውጭ ኢንቨስትመንት ላይ ጥገኛ ሆኖ መቀጠል ተገቢ ስላልሆነና ተወዳዳሪ የሆነ የሀገር ውስጥ ባለሃብት ማሳተፍና መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተጀመረው ስራ ውጤት እያመጣ ይገኛል። ሀገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅማቸው አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸው ውጤት እያስመዘገበ እንደሆነ አመላካች ነው።

‹‹ሀገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገቡ ያስደስታል›› የሚሉት አቶ አክሊሉ፤ ‹‹ሀገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅማቸውና ተወዳዳሪነታቸው ማደጉን ከማመላከቱም በተጨማሪ የውጭና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች በሽርክና (Joint Venture) የሚሰሩበት የቢዝነስ ሞዴል እድገት እያሳየ እንደሆነም ጠቋሚ ነው›› ብለዋል።

በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየር አይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) ለ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ በሰጡት ማብራሪያ፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ጥያቄ ሊነሳበት የማይገባ ጉዳይ እንደሆነና ተጨባጭ ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ተናግረዋል። ባለሀብቶቹ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የወጪ ንግድን በመጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ ስለሚኖራቸው ይህን ሚናቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ በመንግሥት ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ገልፀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጥረት በብዙ መልኮች ሊገለፅ ይችላል። ባለሀብቶቹን የሚያበረታቱ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን በመቅረፅ፣ ፋይናንስን ጨምሮ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት እንዲሁም ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ማድረግ ይቻላል።

እንደ ሞላ (ዶ/ር) ገለፃ፣ በተለይ ኢትዮጵያ በስራ አጥነትና በዋጋ ንረት እየተፈተነች ባለችበት በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው። የመንግሥት ድጋፍ ምጣኔ ሀብቱን በማነቃቃት፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የገቢ ንግድ እቃዎችን በመተካት፣ የወጪ ንግድን በማሳደግ ጥቅል ሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንዲኖረው ያደርጋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል የግብዓቶች (መሰረተ ልማቶች) አለመሟላት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ዋናዎቹ እንደሆኑ ጠቁመው፤ መንግሥት የአጭር ጊዜ መፍትሄዎችን ጨምሮ የባለሀብቶቹን ችግሮች ለማቃለል የሚረዱ የፖሊሲና የመዋቅር እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚኖርበትና ለባለሀብቶቹ የሚያደርገውን ድጋፍ በየጊዜው መገምገምና ማሻሻል እንዳለበትም ገልጸዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ሀገር በራሷ አምራቾች ላይ እንድትተማመን ያስችላል። ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ከሚከሰት አደጋ ለመዳንም ይረዳል። በዚህ ረገድ ሞላ (ዶ/ር) ‹‹የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በፋይናንስና በቴክኖሎጂ አቅም ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ ምጣኔ ሀብታዊ ስብራትና ክፍተት እንዳይፈጠር ለማድረግ ያግዛል። ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉት የውጭ ኩባንያዎች በሀገር ውስጥ የሚቆዩት የሀገር ውስጥ ፖለቲካው እስከተመቻቸው ድረስ ነው። ፖለቲካው ሳይመቻቸው ቀርቶ ኩባንያዎቹ ከሀገር ቢወጡ ሀገሪቱ በርካታ ዓመታት እንደገና ወደኋላ እንድትመለስ የሚያደርግ አደጋ ይከሰታል። ስለሆነም ይህን ስጋት ለማስወገድ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ አቅማቸውን እንዲጎለብቱ ማድረግ ያስፈልጋል›› ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ ‹‹በምጣኔ ሀብታቸው የበለፀጉት የዓለም ሀገራት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን ቀደም ባሉት ጊዜያት ብቻም ሳይሆን አሁንም ከፍተኛ ድጋፍና ጥበቃ ያደርጉላቸዋል። ሀገራቱ በፋይናንስ አቅርቦትም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ለባለሀብቶቻቸው የተለየ የድጋፍ መርሃ ግብር አላቸው። የበለጸጉት ሀገራት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸው የሚያደርጉት ድጋፍ፣ ገና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ከሚያደርጉት ድጋፍ ቢበልጥ እንጂ አያንስም›› በማለት ገልፀዋል።

መንግሥት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ሀገራዊ ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው። የማምረት አቅምን ማሳደግ፣ ለዜጎች ተጨማሪ የስራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እና ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን ማዳን ከ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› መርሃ ግብር የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ንቅናቄው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በማቃለል ረገድ አወንታዊ ሚና እንደሚኖረው ገልፀዋል። የማምረት አቅምን በማሳደግ የወጪ ንግድን ለመጨመርና ገቢ ምርቶችን ለመተካት ለሚደረገው ጥረት አወንታዊ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሆነም ተናግረዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት በንቅናቄው በኢንዱስትሪ ደረጃ ከተለዩ ሁለት ሺህ 167 ችግሮች (የግብዓት፣ የመሠረተ ልማት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት፣ የመስሪያና የማስፋፊያ ቦታ ዝግጅት፣ የጉምሩክና የሎጂስቲክስ አገልግሎት … ችግሮች) መካከል፣ አንድ ሺህ 34 የሚሆኑት መፍትሄ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በቀሪዎቹ አንድ ሺህ 133 ላይ ደግሞ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝና ችግሮቻቸው ከተፈቱላቸው አምራቾች መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ አምራቾች መሆናቸውን አቶ መላኩ ገልፀዋል። ከንቅናቄው ምሠሦዎች መካከል አንዱ የሀገር በቀል ምርቶችንና አመራረትን ማሳደግ መሆኑን ጠቅሰው፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ሳይደግፉ ይህን ማሳካት እንደማይቻል አስረድተዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ሀገር በራሷ አምራቾች ላይ እንድትተማመን ያስችላል። አምራችነቱን ያላሳደገ እና ፍላጎቱንና አቅርቦቱን በራሱ የማምረት አቅም ላይ ያልመሰረተ ምጣኔ ሀብት ደግሞ ዘላቂ እድገትን ሊያስመዘግብ አይችልም። ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ከሚከሰት አደጋ ለመዳንም ይረዳል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት እንድታስመዘግብ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ተወዳዳሪ ማድረግ ይገባል።

‹‹የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ›› እንዲሉ፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍና ተወዳዳሪ የማድረግ ጉዳይ በምጣኔ ሀብት ትብብርና በእርዳታ ስም የሚደረግን የሀብታም ሀገራትንና ተቋሞቻቸውን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት ሉዓላዊነትን እስከማስከበር ድረስ የዘለቀ ትርጉምና ፋይዳ አለው። ሀገራዊ የማምረት አቅምን በማሳደግ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትን ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ደግሞ ሁነኛው መፍትሄ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዋነኛ ተዋንያን እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

# ጎሜ

# በደላላ የሚዘወር ኢኮኖሚ እስከመቼ?

**ስምስም መንግሥቱ**

ጎረቤታሞቹ ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ በጉርብትና ረጅም ጊዜ በመቆየታቸው አንዳቸው የሌላኛቸውን ገመና እስከመሸፈን ደርሰዋል። መኝታ ብቻ ነው የሚለያቸው። አንዷ ቤት ቁርስ ከተበላ፣ ሌላኛዋ ጋር ደግሞ ምሳ ይበላል። እራቱም እንደሁኔታው በአንደኛው ቤት ይሆናል። ጓዳዬ ጓዳሽ መሶብሽ መሶቤ፤ አንች ትብሽ እኔ እብስ ተባብለው ነው ተሳስበው በጋራ የሚኖሩት። የሁለቱ መተሳሰብ ለልጆቻቸውና ባለቤቶቻቸውንም አቀራርቧል።

ሁለቱም ለፍቶ አዳሪ ናቸው። የቀን ገቢያቸው የእለት ኑሮአቸውን ስለሚሸፍንላቸው ኑሮን አማረው አያውቁም። የተትረፈረፈ ኑሮ እየኖሩ ባይሆንም ባላቻው ፈጣሪያቸውን አመስግነው አንዳቸው የሌላኛዋን ጓዳ ሸፍነው በፍቅር ነው የሚኖሩት። ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ጎረቤታሞች ይሁኑ እንጂ አኗኗራቸው የአንድ ቤተሰብ ያህል ነው።

ጎረቤታሞቹ ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ጉርብትናቸው ዛሬ ላይ እንደትናንቱ እየሆነ አይደለም። የነበራቸው ደስታ እየራቃቸው ነው። የየእለት ጨዋታቸውም በምሬት የተሞላ ሆኗል። ይህ የሆነው በመካከላቸው ፀብ ተፈጥሮ አይደለም። የኑሮው ሁኔታ ነው። ቡና ለመጠራራት እንኳን አቅም እያጡ ነው። ለፍቶ ማደሩም እየሆነላቸው አይደለም። የሚሰራው ስራና የሚገኘው ገቢ አልመጣጠን ብሏቸው ነው ይሄ ሁሉ ምሬት።

በቀን ስራ የሚያገኙት ገንዘብ እንደበፊቱ ቁርስ፣ ምሳ እራት በጋራ ሊያቋድሳቸው ቀርቶ የራሳቸውንም ጓዳ እየሞላላቸው ባለመሆኑ ነው መሬታቸው የጨመረው። መሽቶ ሲነጋ ነጋዴውን ማማረር ሆኗል ስራቸው። ከጥንቱም ቢሆን ለነጋዴው ጥሩ አመለካከት የላቸውም። እንዳሁኑ ኑሮ ሸክም ሆኖባቸው አያውቅም። ሌላ ነገር ለማሰብ እንኳን አላስቻላቸውም። በልቶ ለማደር እየተጨነቁ ነው። ይህን ሁሉ እየፈጠረባቸው ያለው ነጋዴው ነው ብለው ያስባሉ።

ጎረቤታሞቹ ባይሉም ነጋዴውና ሸማቹ አይንና ናጫ ከሆነ ከራርሟል። ከጥንቱም ፍቅር ባይሆኑም የአሁኑ ብሷል የሚሉ ጥቂት አይደሉም። ጊዜው ጥንት ለመባል ገና ነው። ግን ዓመታት ተቆጥሯል። በአንድ የአገልግሎት እቃ ላይ ነጋዴው አንድ ብር የማይሞላ ጭማሪ ነበር የሚያደርገው። ጭማሪውም እንደዛሬው መሽቶ ሲነጋ አይደለም። ኸረ እንደውም አንዳንዴ መሽቶም አይነጋም በሰዓታት ልዩነት ነው የዋጋ ጭማሪው። ታዲያ በያኔው በዓመታት ጊዜ የዋጋ ጭማሪ ሲደረግ በሸማቹ በኩል የሚሰማው ሮሮ አይጣል ነው። አለፍ ሲልም ነጋዴው ይረገማል።

በያኔው መንግስትም በነጋዴው ላይ ይወስድ የነበረው እርምጃ ቆንጠጥ ያለ ነው ይባላል። እርምጃው እግር ተወርች እስከማሰር የደረሰ ነው አሉ። መንግስት ዋጋ እንደፈለገኝ እጨምራለሁ ላለ ነጋዴ ውርድ ከራሴ ስላለ በአንድ እቃ ላይ የሳንቲም ጭማሪ ለማድረግ እንኳን ዛር ወጥቶ ዛር ተንቀጥቅጦ ነው። ታዲያ የዚህ ዘመን ነጋዴ የሸማች ዐይን እየበላው አፍጥጦና አግጦ የሸማች ጫንቃ የማይሸከመውን ዋጋ መቆለሉ ከምን የመጣ ነው? ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ የሶስትና አራት እጥፍ ጭማሪ መደረጉ ነው።

ነገሩ ሁሉ ያበቃው አንድ ኪሎ ሽንኩርት መቶ ሃምሳ ብር ማውጣቱ፣ የአንድ ኪሎ ጤፍ ዋጋ ከ120 ብር ሲዘል፣ እንደው ምንም የሌለው የነጣ ደሀ የሚመገበው የበሰለ ሽሮ ወጥ በአንድ እንጀራ 100 ብርና ከዚያ በላይ ሲሸጥ ነው። አንድ ጫማ ሰፊ በአንድ ጅማት አንድ ጫማ ዙሪያውን ሰፍቶ 50 ብር ሲቀበል ነው እጅዎን በአፍዎ ላይ ለማድረግ የሚገደዱት።

ጫማ ሰፊው ያስከፈለው ለጅማቱ ላወጣው ወጪ፣ ወይንም ለጉልበቱ አይደለም። በአንድ እንጀራ ሽሮ ፈሰስ ለሚጠየቀው ዋጋ ነው። ለዚያውም ሁለት ጫማ ሰፍቶ ከሆነ ነው መብላት የሚችለው። ለነገሩ ድሮ በአምስት ሳንቲምና አስር ሳንቲም ይሸጥ የነበረው የጫማ መስፊያ ጅማት አንዱ አምስት ብር ገብቷል። አሁን እኮ የሳንቲም ዘሮችን ካየን ቆየን። አምስትና አስር ሳንቲም ያለው ሰው ሳይሸለም ይቀራል። አስር ብር አንድ ዳቦ እንኳን ለመግዛት ባለመቻሉ አይደል የኔ ቢጤ ሳንቲም ለመቀበል ቅር የሚሰኘው።

የዋጋ ነገር ስንቱ ተነስቶ ስንቱ ይቀራል። የሰው ልጅ ለፍቶ የሚፈጥረው ገንዘብ የተገላቢጦሽ እራሱን ዋጋ እያሳጣው ነው የመጣው። የሰው ልጅና ገንዘብ ሚዛን ላይ ቢወጡ ሚዛኑ ፍታዊ ከመሆን ይልቅ ወደ ገንዘቡ ነው የሚያደላው።

የኑሮ ውደነቱ ጎረቤታሞቹ ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። የብዙዎችን የእርስበርስ ግንኙነት ነው ያሻከረው። ጎረቤታሞች አንዱ መገናኛቸው ቡና ጠጡ ነው። ቀደም ሲል የአንድ ኪሎ ቡና ዋጋ እዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ አንድ ቤት በቀን ሶስቴ ነው የሚፈላው። ቡና ቁርሱም ቢሆን አይሰሰትም። ማኅበራዊ ትስስሩ፣ አንድነቱ፣ አብሮነቱ፣ መተሳሰቡ የሚመጣው በቡና ጠጡ ነው። ፖለቲካውም ቢሆን፣ ስለሚነሳ ሰዎች በዚህ አጋጣሚ የተለያየ አመለካከት ይኖራቸዋል። የኑሮ ውድነቱ ይሄን ሁሉ ነው እንደ ፈንጂ እየበተነ ያለው።

በተለይም ኅብረተሰቡ በዕለት ተዕለት በሚጠቀምባቸው መሰረታዊ ፍጆታዎች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዜጎችን ሕይወት እጅግ እየተፈታተነው ይገኛል። በእህል፣ በጥራጥሬ፤ በአትክልት ምርቶች፤ በግንባታ ዕቃዎች እና በቤት ኪራይ ላይ የዋጋ ጭማሪው አሳሳቢ ሆኗል። ነገሩን ይበልጥ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ከፍተኛ የዋጋ ግሸበት እየተመዘገበ ያለው የምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ መሆኑ ነው። ትራንስፖርት፣ የትምህርት ቤት ክፍያና የመሳሰሉት ሲጨመሩበት የሕዝቡን ኑሮ ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ እያደረገው ነው፡፡

በየቀኑና በየሰዓቱ የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ በተለይም ዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል ኑሮ እንደምርጊት እንዲከብደው ምክንያት ሆኗል። መሽቶ በነጋ ቁጥር «ከገበያ ጠፍተዋል»፤ «ዋጋ ጨምሯል» የሚሉት አገላለጾች ኅብረተሰቡን በሰቆቃ ውስጥ እንዲኖር እያደረጉት ነው፡፡

የኑሮ ውድነቱ እንቆቅልሽ አልፈታ ያለው በምን አይነት ገመድ ቢተበተብ ነው። ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል አሉ። እጃቸውን ታጥበው፣ ያማራቸውን እየበሉ፣ በውስኪ እየተራጩ፣ አማርጠው እየለበሱ ሽሮ እንኳን እሮባቸው እጃቸውን ለልመና በዘረጉ በራሳቸው ወገን ላይ የሚጨክኑ መኖራቸው ለሰሚም ግራ ያጋባል። እንዲህ ያለውን ሚና የሚጫወቱት ደግሞ ደላሎች ናቸው የሚለው ወቀሳ የበዛ ነው።

እነዚህ ደላሎች እውቅና የተሰጣቸው እስኪመስል ድረስ በመካከል ላይ ሆነው የሚደልሉ ሕገወጦች ስለመኖራቸውና ለኑሮ ውድነቱም ምክንያት እንደሆኑ በመንግስት ስልጣን በያዙ ሰዎች ሳይቀር በየጊዜው ሲነገር ይሰማል። የሰው ጆሮም እየለመደው በመምጣቱ ሕገወጥነታቸው ቀርቶ ሕጋዊነታቸውን የሚያረጋግጥ እየመሰለ ነው። ይህን ስሜት የፈጠረው መደጋገሙ ነው።

ደላላ እስከሚታወቀው ድረስ አገናኝ ነው። ሥራውም ባገናኛቸው ሰዎች መካከል ሆኖ ተግባብተውና ተስማምተው እንዲገበያዩ ወይንም የተገናኙበትን ጉዳይ እንዲፈጽሙ ማስቻል ነው። ለስራውም ሕጋዊ በሆነ መንገድ ክፍያ ያገኛል። አሁን የሚባለው ደላላ ግን አገናኝ ሳይሆን፣ ወሳኝ ነው። ማረሻና መሬት ማገናኘት ምን ማለት እንደሆነ እንኳን በቅጡ ሳያውቅ ነው ማሳ ላይ ያለውን ምርት ዋጋ ወስኖ ገበያ ላይ እንዲውል የሚያደርገው። ገበሬው የእርሱና የልጁ ጉልበት አያሳስበውም። የማምረቻ መሳሪያ ዋጋ መጨመር፣ የማዳበሪያ ወጪ፣ የከብት መኖ፣ የውሃ አቅርቦት ነው ትልቁ ጥያቄና ፈተናው።

የተፈጥሮ ዝናብ ለማግኘትም አንገቱን ወደፈጣሪው አንጋጦ የሚለምነው ይኸው ገበሬ ነው። በዚህ ሁሉ ልፋት ውስጥ ሆኖ ያመረተውን ምርት ሸጦ የድካሙን ለማግኘት በራሱ አይወስንም። በነዚህ ደላላ ተብዬዎች እጅ ይወድቃል። የእለት ጉርሱም፣ የዓመት ልብሱም ባመረተው ምርት ላይ የሚወሰን በመሆኑ መሸጡ ግድ ነው። የገበሬውን የውስጥ ገመና በማወቅ የተካኑት ደላሎች ያለምንም ርህራሄ በድካሙ ገብተው እነሱ ይከብሩበታል።

ደላሎቹ በቅድሚያ በወሬ አምራቹን የሚያዳክም ስራ ነው የሚሰሩት። በሚነዙት ፕሮፓጋንዳ የዋጋ ማጣጣል ብቻ ሳይሆን የሚሰሩት፤ ምርቱንም ካቆየው ገበያ እንደማያስገኝለት ጭምር በመሆኑ አምራቹ ለመሸጥ አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ ያደርጉታል። እነዚህ ደላሎች ሀገርንም ነው ፈተና ውስጥ የከተቱት። የብር የመግዛት አቅምን ብቻ ሳይሆን እያዳከሙ ያሉት የፖለቲካ ኪሳራም እያስከተሉ ነው። ዛሬ ገበያው የሚመራው በመንግስት አቅም ሳይሆን በደላላ ነው የሚለው ትችት እየበረታ የመጣውም ይኸው ሰው ያወቀው፣ ፀሀይ የሞቀው የደላሎች እንደልብ መፈንጨት ነው።

የደላሎች ጉዳይ ሕዝብንም ጥርጣሬ ውስጥ እየከተተው ነው። አይዟችሁ በርቱ የሚሉ የመንግስት ሹመኞች ይኖሩ ይሆን? መቼም በጎን ከነርሱ ጎን ቆመው፤ ለሕዝቡ እነዚህን ያለፉበትን ያልደከሙበትን ቁጭ ብለው የሚበሉ ሕገወጥ ደላሎች ከገበያው መካከል እናወጣቸዋለን ብለው ለሕዝብ በግልጽ አይናገሩም። ደግሞ እነርሱን ለማዳከም የእሁድ ገበያ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በአራት አቅጣጫ ገበያ ተከፍቷል። እነርሱም ገበያውን እንዲያረጋጉ በቁጥጥርና በክትትል የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል። ነገሩ አንዱን ቀዳዳ ሲደፍኑ ሌላው እያፈሰሰ ነው እንደሚባለው ይሆን? ወይንስ እውነቱ ገና አልተገለጠልንም፡፡

ለመሆኑ እነዚህ ደላሎች ሀይ ባይ ያጡት ለምንድነው? መንግስትም አማራጮችን ለሸማቹ ከማቅረብ በዘለለ ሕዝብን የሚያስደስትና እፎይ የሚያስብል ደላሎቹን የሚያዳክም ሁነኛ እርምጃ ሲወስድ አይስተዋልም። ነገሩ ግራ ያጋባል። ሰፊ መሬት፣ ተስማሚ የአየር ጸባይና ስነ ምህዳር፣ ርካሽ ጉልበት አላት በምትባል ሀገር የተትረፈረፈ ምርት አምርቶ ዜጋውን አጥግቦ ለሌላው መትረፍ ያልተቻለው ለምን ይሆን? በደላላ የሚዘወር ኢኮኖሚ እስከመቼ ነው የሚዘልቀው የሁላችንም ጥያቄ ነው?

ከሰሞኑ አንድ ኪሎ ሽንኩርት ከ150 ብር ወደ 80 ብር በመውረዱ ሸማቹ ፈጣሪውን እያመሰገነ ነው። ምስጋናው ውሎ አያድርም። ለመገናኛ ብዙሀን ፍጆታ ከዋለ በኋላ ወደነበረበት ይመለሳል። ይህ እስከ መቼ ነው የሚቀጥለው። ኢትዮጵያ ውስጥ ምርት በደረሰ ጊዜም ሆነ ምርት በሌለበት ወቅት የመሸጫ ዋጋ ልዩነት ሳይፈጥር ዓመታት ተቆጥሯል። ዛሬም ይኸው ነው የሚታየው። እናስ በዚህ ሁኔታ የምንቀጥለው እስከ መቼ ነው?

> **ነገሩ ሁሉ ያበቃው አንድ ኪሎ ሽንኩርት መቶ ሃምሳ ብር ማውጣቱ፣ የአንድ ኪሎ ጤፍ ዋጋ ከ120 ብር ሲዘል፣ እንደው ምንም የሌለው የነጣ ደሀ የሚመገበው የበሰለ ሽሮ ወጥ በአንድ እንጀራ 100 ብርና ከዚያ በላይ ሲሸጥ ነው። አንድ ጫማ ሰፊ በአንድ ጅማት አንድ ጫማ ዙሪያውን ሰፍቶ 50 ብር ሲቀበል ነው እጅዎን በአፍዎ ላይ ለማድረግ የሚገደዱት**

# የዘመን ጥበብ

## ስውሯ እጅ በዓድዋ!

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ስውር እጅ፣ ለማንም ሰው የማትታይ፤ አርበኛውን በጥበብ መንፈስ የምትሰውር። ይህቺ ምትሀት በኢትዮጵያ አርበኞች ዘንድ ነበረች። ለመሆኑ ማናት?፤ እስቲ ለአፍታ እናሰላስላት...በዓድዋ ጦርነት፤ በዱር በገደሉ ሁሉ እየገባች ከአርበኛው ጋር ወድቃ ስትዋደቅ፤ ወግታ ስታዋጋ የነበረችው ይህች ተዓምረኛ እጅ እራሷ ጥበብ ነበረች። እሷም እንዲህ ነበር የምትለው "እናት አባት ቢሞት በሀገር ይለቀሳል፤ ወንድም እህት ቢሞት በሀገር ይለቀሳል፤ ሀገር የሞተች እለት ወዴት ይደረሳል!"

የዓድዋ ድል ሲወሳ፣ የአርበኞች ድል ሲነሳ ኪነ ጥበብ ከተረሳች ነገሩ ሁሉ ተበላሸ። ዓድዋ የቆመበት መሰላል ዘመናዊ የጦር መሳሪያ አሊያም ቴክኖሎጂ ሰራሽ መከላከያ አልነበረም። አንድና አንድ ከአርበኛው ዘንድ የነበረው ነገር የጥበብ እንፋሎት፤ ስውር የኃይል ሚዛን ብቻ ነበር። በእጅ የጨበጡት የጦር መሳሪያ ሳይሆን በልብ ያነገቡት ጥበብ ዘራሽ ወኔና የሀገር ፍቅር ብቻ። ይህ የጥበብ ውለታ እንዴት ይረሳል ብንልም፤ እውነታው ግን ተረስቷል። አሊያም ተዳፍኖ እንዲቀር ተደርጓል። በዓድዋ ሰማይ ላይ፤ የኪነ ጥበብ ውለታ በጦርነቱ ወቅት ብቻ አይደለም። ከዚያም በኋላ የዓድዋ ስሜት ሳይበርድ ሳይባረድ እንደነበረው ሲወርድ ሲዋረድ ዛሬም ድረስ ከነሙሉ ወዘናው እንዲቆይ በማድረጉም ጥበብን የሚስተካከላት የለም።

የዓድዋ ትውስታ በስሜት ማዕበል እንዲንጠን እያደረገ ያለው ነገር ምንድነው? ብለን በመጠየቅ ግራና ቀኝ፤ ኋላና ፊት ብንዞር የምናገኛት ይህችኑ ጥበብን ነው። "ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ" ቢሉ፤ ስለዚህ የኪነ ጥበብ ምትሀት በወቅቱ ከነበሩት አርበኛ አባቶች አፍ ብንሰማውማ እንዴት ያለ የአዕምሮ ልቀትና የጥበብ ብስለት የነበራቸው እንደነበር በቅጡ እንረዳው ነበር። የስውሯን እጅ አደገኝነት እራሱ ፋሽስቱ በአንክሮ ተመልክቶታል።

መጀመሪያ አካባቢ የኢትዮጵያ አርበኞች እንዲያ በግጥምና በአዝማሪው ቅኝት ሲነሆልሉ፤ ሲሸልሉና ሲፎክሩ፤ ቀረርቶውን እየነፉ በጠላታቸው ላይ ሲደነፉ፤ በንቀት ተመልክቶ እንደ እብደት ቋጠሮ ሲስቅ ሲሳለቅባቸው ነበር። ነገሩንም ከቁብ አልቆጠረውም። ይህን ደህና አድርጎ የተረዳው ከሽንፈቱ ማግስት ነበርና ከዓመታት በኋላ ተመልሶ ለዳግም ወረራ በመጣበት ወቅት፤ የበቀል ክንዱን ካሳረፈባቸው ስፍራዎች አንዱ የኪነ ጥበብ መንደር ውስጥ ነበር። ከወደ መርካቶ አካባቢ በነበሩ ቁጥራቸው በውል ባይታወቅም ከ 120 በላይ የሆኑ አዝማሪያንን ሰብስቦ፤ በአንድ ጀንበር ጨፍጭፏቸዋል። በአጋጣሚ የሆነ አይደለም፤ ጥበብ እያታለለች ያጠጣቻቸውን፤ የያኔውን መራራ የሽንፈት ገፈት፤ ጠረኑ ከስሜት አፍንጫቸው ላይ ሽው እያለ በአዕምሯቸው ሲመላለስ ስለነበረ ነው። በዳግም ወረራቸው ወቅት በቀልና ጭካኔን ከእልህ ጋር በጥብጠው የሞትን አሲድ ከአዝማሪዎቹ ፊት ላይ ደፉት። እናስ ከዚህ ተግባራቸው በላይ ለጥበብ ነቃሽ ሆኖ የሚቀርብ ምን አለና።

በጥበብ ቤት፤ በኪነ ጥበብ ጓዳና ሳሎን ዓድዋን የማናገኝበት አሊያም ደብዝዞ የሚታይበት አንድም ስፍራ አናገኝም። ዓድዋ ላይ ጥበብ ነበረች ከማለት፤ ዓድዋ እራሱ ጥበብ ነበር ማለቱ ይቀላል። ትዕይንቱ በራሱ የመድረክ ላይ ትወናና የአንድ የመጽሐፍ ድርሰት እንጂ የገሀድ ታሪክ የማይመስል ነው። ታዲያ ይህ ዓድዋ የሌለበት ኪነ ጥበብ የት አለና...በሙዚቃው ገበታ፤ በቲያትሩ መሶብ፤ በግጥሙ አቁማዳ፤ በልብወለዱ ሰፌድ፤ በስዕሉ ትሪ...በሁሉም ቦታ ዓድዋ ከነመንፈሱ አለ። ምናልባትም ቅር ሊለን የሚችል አንድ ነገር ቢኖርም ከፊልሙ ዘርፍ በአቅም ውስንነት የተነሳ እንደታሪክ ሊቀመጥ የሚችልና ከምንም ጋር ሳይቀየጥ እራሱን ችሎ የተሠራ የሙሉ ጊዜ ፊልም አለመኖሩ ነው።

ከዓድዋ ታሪክ ላይ ተቀንጭበው የተሠሩ አጫጭር ፊልሞች በርከት ብለው ልናገኝ እንችላለን፤ ዘጋቢ ፊልሞችንም እንዲሁ። ነገር ግን በገጸ ባህሪያቱ መሪነት የዓድዋን ሙሉ የታሪክ ትዕይንት ሊያሳየን የሚችል ፊልም እስካሁን ብቅ አለማለቱ ነው። ዓድዋ እንደታሪክ ግዝፈቱ፤ በአንድ ሰዓት ከ45 ደቂቃ አሊያም በ2 ሰዓታት የእይታ ጊዜ ብቻ የምንቋጨው አይደለም። ገቢሮቹ ለቁጥር የሚታክቱ ናቸው። በዚህም እጅግ በበርካታ ምዕራፎችና ክፍሎች የታጨቀ ተከታታይ ፊልም ሊወጣው የሚችል ነው። እንሥራው ቢባል ከሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ከገንዘብ እንዲሁም ከቴክኖሎጂ አንጻር ነገሩ ፈታኝና የማይሞከር ቢመስልም የማይቻልና ተስፋ ቢስ ግን አይደለም። ከልብ



ካለቀሱ እንባ አይገድምና ይህ ለፊልሙ ዘርፍ ባለሙያዎች ሁሉ ትልቁ የቤት ሥራ ነው።

እግረ መንገዳችንን ወደዚህ ሀሳብ ሾልከን ገባንበት እንጂ ዋነኛው ርዕሰ ጉዳያችን ፊልሙ አይደለምና ወደ ጦርነቱ አውድማና ኪነ ጥበብ እንመለስ፡፡

ኸረ ለመሆኑ በዓድዋው የጦር አውድማ ጥበብ እንዴትስ ስውር እጇን አስገባች? ለዚህች ጥበብ የልባቸውን በር ከፍተው ነይ ግቢ ሲሉ ያስገቧት የመጀመሪያው ሰው አጼ ሚኒልክ ነበሩ። ጥበብ ሀገር ምድሩን ሞልታ በየሕዝባቸው ልብ ውስጥ ማደሪያዋን ስለመስራቷ አውቀውት ነበርና የመጀመሪያውን የእናት ሀገርህን አድን ጥሪያቸው በራሱ ኪናዊ ለዛን የተላበሰና ስሜት ቀስቃሽ፤ የሀገር ፍቅርን የሚያሚሽ ነበር። ጊዜው ጭጋጋማውም የክረምት ወራት አልፈው የሀገሬው ሕዝብ " እዮሃ አበባዬ... መስከረም ጠባዬ!" የሚልበት ነበር። ከፈካችው ፀሐይ በታች የሚነፍሰው አየር ግን እንዲህ አልነበረም። የሐምሌ ነሀሴው፤ የጳጉሜው ጭጋግ ሲገፍ፤ ሌላኛው የፋሽስት ጭጋግ 22 ሺህ የሰለጠኑ ወታደሮችና በዘመኑ አሉ የተባሉ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎችን ጭኖ ኢትዮጵያን ሊወር፤ ከኢትዮጵያ ደጅ ላይ ከትሟል።

ከላይ ታቹ ያኮበኩባል። ይህን የወራሪውን ድግስ የተመለከቱት ንጉስ አፄ ምኒልክ ያሰላስሉና መላውን ይዘይዱት ገቡ። ከዚያም 1888 ዓ.ም መስከረም ሰባት ቀን ወደ እንጦጦ ማርያም ደብር ወጡ። ጠላት ለሞቱ ለደገሰው ድግስ ቀባሪውን አርበኛ ጠሩለት።

አጼ ሚኒልክ፤ ስሜት ኮርኳሪውንም የጥበብ ነጋሪት እያስጎሰሙ እንዲህ ሲሉ አወጁ "ድንበር የሚገፋ፣ ኃይማኖት የሚያጠፋ-ተወኝ! ብለው እያደር እንደ ፍልፈል አፈር የሚገፋ ጠላት መጥቷልና፤ የአገሬ ሰው እስከ ዛሬ ያስከፋሁህ አይመስለኝም፤ እኔንም አስከፍተሽኝ አታውቅምና ዘመቻ በየካቲት ስለሆነ _እስከ ጥቅምት እኩሌታ ወረኢሉ ከተህ ላግኝህ" በማለት ወደ ክተት ዘመቻው እንዲገባ ለሚወዳቸው ሕዝባቸው መልዕክቱን ሰደዱለት። የሚመጣውም ለንጉሡ ዘፋን ብሎ ሳይሆን ለራሱ ሲል መሆኑን እንዲያውቅና እንዳይቀር ሲሉ ደግሞ የሕዝባቸውን የልብ ትርታ ያውቁታልና በማያስነካው መጡበት። ሀገሩን ለሚወድ ስለ ሀገሩ፤ እርስት ያለው ስለ እርስቱ፤ ትዳር ያለው ስለ ሚስትና ልጆቹ፤ በኃይማኖቱ የማይደራደረውም ስለ ኃይማኖቱ ሲል ጠላቱን እንዲዋጋ ፍም እሳቱን ከቆሰቆሱት በኋላ በመጨረሻም ከሁሉ ወጥቶ አንድ ለቀረው "ወስልተህ የቀረህ እንደሆን... ማርያምን አልምርህም!" በማለት ከልቦናው አቆራኙት።

ይህን ሰምቶ የቀረ አልነበረም። ለቁጥር የሚታክት፤ ለአይንና ለጆሮ የማይታመን ሕዝብ፤ ከአራቱም አቅጣጫ፤ ጨርቄን ማቄን ሳይል ከእጁ የገባውን አፈፍ አድርጎ ይተም ጀመረ። ያውም ነጭ በነጭ፤ የክት ልብሱን ለብሶ ለሠርግ እንጂ ለሞት ድግስ የሚሄድ እስከማይመስል ድረስ በአንዳች ኃይል ተሞልቷል፡፡

ጥበብም ይሄኔ ነበር፤ ቁጣው የነብር የመሰለውን ጥቁር ሕዝብ ተመልክታ፤ እኔስ ለምን እቀር ስትል በሶምሶማ እየተከለች ወደ ዘመቻው መግባቷ። ስውሩን እጅ ታምረኛውን መዳፏን፤ በእያንዳንዱ አርበኛ የልብ ደም ስር ላይ ቀረጸችው። አርበኛው ያንን የሚያህለውንና በዘመናዊ ጦር ታጥቆ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለውን የፋሽስት ጦር ለመውጋት ቀርቶ ለመመከት እንኳን የሚሆን መሳሪያ ከእጁ አልነበረም። እርሱ ዘንድ የነበረው ነገር ቢኖር የሀገር ፍቅር፤ ወኔ፤ ጀግንነት፤ የልብ እሳትና መለኮሻው ጥበብ ብቻ ነበር። ታዲያ ይህን ይዞ በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ሞት ካነገበ ፋሽስት ጋር ለመጋጠም መወሰን እብደት አይደል? ፈረስ ላይ ተቀምጦና ለአደን የሚጠቀማትን የእጅ ጦር ይዞ፤ ከፊት ወደቆመው ታንከኛና መድፈኛ መገስገስ፤ ይሄስ ምን ይሉታል? ፋሽስቶቹ እራሳቸው እየተሳለቁ፤ "እኚህስ እብድ ናቸው" ብለውታል። ላዩን ለተመለከተማ እውነትም የእብደት ጥግ ይመስል ነበር። የሀገሬው ጀግና ግን ሙያ በልብ ብሎ፤ ከልቡ የታጠቀውን ማንም አላየም። ሞት የጎረሰው፤ የታንክ አፈሙዝ ከግንባሩ ተደግኖ እያየ፤ እሱ ግን እረቂቁ የጥበብ ኃይል ሰይፈው ባለችው ቁጥር፤ አይኑን ጨፍኖ በሀገሩ ፍቅር በተሰወረው ልቡ እየተመለከተ፤ ያ ሁሉ የተሰለፈው የጠላት ወታደር እንደ ገብረ ጉንዳን፤ ታንክና መድፉም እንደ ርችት መስሎ ይታየዋል። እናም ጎራዴውን ይዞ እየፎከረና እየሸለለ አንድ ወደፊት ይሄድና እልፍ ዘርሮ ይመለሳል።

ለሀገሩ ሲል ሞትም ሕይወት ስለመሆኑ፤ በጥበብ ያደረች ነብሲያው ነግራዋለችና ስለምንም አይፈራም ነበር። ከአርበኛው ውስጥ ያለው ክብል የጥበብ ኒውክሊየር ቦንብ እየፈነዳ ጠላትን ይረመርመው ቀጠለ።

በጦሩ አውድማ የአዝማሪያኑ የወኔ ጦማር ገዘፍ ያለ ነበር። ጀግና ሲሞት፤ ጀግና እየተኩ ይበልጥ ያጀግኑታል። "ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ፤ መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ።" እያሉ ሲዋድሱ የሰሙት ባልቻ አባ ነፍሶ፤ ስውሯ እጅ ሄዳ የልብ ግርግዳቸውን ብትኮረኩር ጊዜ፤ እሳቱን ለኩሰው ሄደው የሰላቶውን ጦር የአመድ ክምር አደረጉት። በእያንዳንዱ የጠላት መውደቅ ውስጥ ስውሯ ጥበብ የወለደችው፤ የኪነ ጥበብ መርፌ ነበረበት። ይህን ጉድ የተመለከተ ነጭ ሁሉ፤ "ኢትዮጵያውያን፤ ቀድሞም ለጦርነት የተፈጠሩ ሕዝቦች ናቸው" ሲል በራሱ አንደበት መስክሮላታል፡፡

ጦርነት ማለት የታንክና የመድፍ ኳኳት ብቻ አለመሆኑንም የጦር ልሂቃኑ አርበኞቻችን በሚገባ አስተምረውታል። እንግዲህ ሰላቶውን ምን ይዋጠው... የሀፍረት ሸማውን እንደተከናነበ፤ ጅራቱን እንደተመታ ውሻ ጭራውን ቆልፎ ተመለሰ፡፡

**ዓድዋ ትላንት ዓድዋ ዛሬ**

ከጥበብ ታዛ በታች ዓድዋ ትላንት ዓድዋ ደግሞ ዛሬም ናት። ትላንት ባዶ እጁን ለወጣው ጀግና አርበኛ ስንቅ የነበረው ኪነ ጥበብ ዛሬም ደሙ አልቀዘቀዘም። በክረምቱ ከአዋሽ እስከ በሽሎ ወንዙ ሁሉ ሲሞላ፤ ባህሩን ከፍላ ዓድዋን ያሳለፈችው ያቺ ስውር የጥበብ እጅ፤ ዛሬም በበጋው ክንዷ ሳይዝል ዓድዋን እንደታቀፈችና እንዳዘለች አለች። ማየት ተስኖን አሊያም ላለማየት ፈልገን ካልሆነ በስተቀር ይህ አሁንም ይታያል። ዓድዋን እያወሱ መዘከሩን ኪነ ጥበብ ለአፍታ ዘንግቶት አያውቅም። አብነት ለሙዚቃ፤ የትላንትናው የአርበኞች ወኔና የሀገር ፍቅር ወላፈን ዛሬም ከልባችን፤ በጥበብ እንፋሎት እንዲንቀለቀል ያደረጉ ብዙ ቢኖሩም ሁለቱ ግን በልዩነት የሚነሱ ቁንጮ ናቸው። እነርሱም እጅጋየሁ ሽባባው (ጂጂ) እና ቴዎድሮስ ካሳሁን(ቴዲ አፍሮ) ናቸው፡፡

ሁለቱ ከያኒዎች ትላንትናን እንደዛሬ አድርጎ በማንጎራጎር፤ ዓድዋ ትላንትን ዓድዋ ዛሬ አድርጎ በማሳየት ማን እንደነርሱ ተብሎላቸዋል። ጂጂ "ትናገር ዓድዋ" በሚለው የሙዚቃ ሥራዋ አድናቆትን ብቻም ሳይሆን ልዩ የሆነ የትውስታ አሻራዋን ዓድዋን ከኪነ ጥበብ አዛምዳ አስፍራለች። የየካቲት 23 ቀን የዓድዋ መታሰቢያ የሆነችው፤ ይህቺ ልዩ ቀን እየቀረበች በመጣች ቁጥር "ትናገር ዓድዋ" የጂጂን ድምጽና መልክ ይበልጥ እያጎላች ትመጣለች። በዚህ ሰሞን ይህን ሙዚቃ አለመስማት ቅር ቅር ያሰኛል። ቢሄዱ በመንገድ፤ ቢቀመጡ በወንበር፤ ጆሮ ግን "የተሠጠኝ ህይወት ዛሬ በነፃነት፤ ሰው ተከፍሎበታል በደምና በአጥንት" የሚለውን ዜማ ሲንቆረቆር ለመስማት ይናፍቃል። በሙዚቃው ውስጥ ያሉ ስንኞች የዓድዋን የመስዋዕትነት ጥግ የሚያሳዩ ናቸው።

ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከነ ክብር ወዘናዋ እንድትኖር የተከፈለው "ዋጋ" በሚል ቃል ብቻ የሚገለጽ አለመሆኑን ለማመልከት "ሰው ተከፍሎበታል" ስትል ድንቅ አገላለፅና ጠንካራ ቃላት ተጠቅማዋለች።

በዓድዋ ትላንት በዓድዋ ዛሬ፤ የጥበብን እጅ ስሞ ባንዲራዋን የተቀበለው ሌላኛው ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ነው። "ጥቁር ሰው" በሚለው ሙዚቃው፤ የዓድዋን ትኩስ ደም ከደማችን አዋህዶታል።

...

"ዳኘው ያሉት አባ መላ ፊት ሃብቴ ዲነግዴ
ሰልፉን በጦር አሰመረው ፊት ሆኖ በዘዴ"

...

"ዓድዋ ሲሄድ ምኒልክ ኑ ካለ
አይቀርም በማርያም ስለማለ"

...

"አባቴ ምኒልክ፤ ድል አርጎ ሰራው የእኔን ልክ
ጊዮርጊስ ፈረሱ ላይ፤ ቆሞ ሳይ ድል ቀናኝ ሳልል ዋይ"
አባቴ ወኔውን ተኮሰው ምኒልክ ጥቁር ሰው" ...እያለ ይቀጥለዋል። የዚህን ሙዚቃ የቪዲዮ ክሊፕ ለመሥራት፤ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የሰው ኃይል ተጠቅሟል። ወጪ የተደረገበት የገንዘብ መጠንም የሙዚቃውን ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ክብረ ወሰን የሰበረ ነበር። ሥራውን ከልቡ ሠርቶታል። በዓድዋ ትላንት በዓድዋ ዛሬ፤ እኚህን ሁለቱን ፈርጦችን ጨምሮ፤ በግጥምና ስነ ጽሁፉ፣ በስዕሉ፣ በቲያትሩ፣ በሙዚቃው፣ በፊልሙ እንዲሁም በተቀሩት ሁሉ "እናመሰግናለን!" የምንላቸው ብዙዎች አሉን።

ስለ ዓድዋ የባህረ ሀሳብ ረቂቅ ባይዘጋጅለትም የሚለው ግን ይህንን ነው...በጦርነት ውስጥ፤ አሸናፊ ለመሆን ወሳኙ ነገር የስነ ልቦናና የአዕምሮ ረቂቅነት እንጂ የዘመናዊ ጦር ልህቀት አይደለም። ቀለህና ፈንጂ ከመቀመም ይልቅ የማይታይና የማይጨበጠውን ውስጣዊ መሳሪያ መፈብረክ ብልህነት ነው። ኒውክሊየርና ሚሳኤል ከማስወንጨፍም፤ ስውሯን የስሜት ቦንብ በደም ስር ውስጥ መቅበር ይበልጣል። እናም፤ በዚህ የጦር ታክቲክ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ አርበኞች ልብ ውስጥ የተሾመችው ጀነራል፤ ጥበብ ነበረች። ጥበብም ግዳጇን በአግባቡ ፈጸመችው። ክብር ለዓድዋ ጀግኖች!! ክብር ለስውሯ የጥበብ እጆች!!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ማኅበሩ የዓይነ ስውራን ሴቶችን ሕይወት ለማቅናት ድጋፍ ይሻል

**እየሩስ ተስፋዬ**

ከመጀመሪያ ደረጃ ተማሪነቷ ጀምሮ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃ እስከትወጣ ድረስ በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በቅርቡ ተመርቃለች። ዛሬም ቢሆን የችግሩ ዓይነት ይለይ እንጂ ፈተና ላይ ናት። ዓይነ ሥውሯ መስከረም መኩሪያ፣ ሥራ ለማግኘት ቀጣሪ ድርጅቶችን ደጅ ብትጠናም አልሆነላትም። ግራ ቢገባት ለምታውቃቸው ሁሉ ‹‹የሥራ ያለህ?›› እያለች ነው። ዘወትር ሥራ እንዲፈልጉላት የምታውቃቸውን ሰዎች በመማጸን ላይ ትገኛለች።

ይህ ዓይነቱ ችግር የመስከረም ብቻ ሳይሆን የብዙ ዓይነ ሥውር ሴቶች ችግር ሊሆን እንደሚችል ነጋሪ አያሻውም። ዓይነ ሥውራን በብዙ ነገር አለመመቻቸት በየቀኑ ከሚገጥማቸው ፈተናዎች አንዱ የሥራ ዕድል ማግኘት ጎልቶ ይነሳል።

ብራይት ወርልድ ፎር ብላይንድ ውሜን አሶሴሽን (ማኅበር) ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ማኅበር ሲሆን የሴት ዓይነ ሥውራንን ችግር ለማቅለል ጥረት ያደርጋል። ሴት ዓይነ ሥውራን በጎ አድራጊ በሆኑት በወይዘሮ አዳነች ቸኮል አማካኝነት በ2005 ዓ.ም ብዙ ዓላማ ሰንቆ ነው የተቋቋመው። ከዓላማዎቹ መካከል ሴት ዓይነ ሥውራንን ማሰልጠን፣ በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል፣ ከጥገኝነት እና ከልመና ማላቀቅ አንዱ ነው።

የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ዘነበች በላቸው እንደሚናገሩት፣ ማኅበሩ ከሚሰጣቸው ሥልጠናዎች መካከል የብሬል፣ የኮምፒውተር፣ ለወጣት ሴቶች የሥነ ተዋልዶ፣ ኤች አይቪ/ኤድስ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የሕይወት ክህሎት ሥልጠና ተጠቃሾቹ ናቸው። ማኅበሩ በሦስት መንገዶች ለሴት ዓይነ ሥውራን አባላቶቹ ድጋፍ እንደሚያደርግ የጠቆሙት ሥራ አስኪያጇ፤ አንደኛው በዕድሜ የገፉና አቅመ ደካማ የሆኑ ሴት ዓይነ ሥውራንን፣ ከቤት መውጣት



ማኅበሩ የሴት ዓይነ ስውራንን ሕይወት ለማሻሻል ድጋፍ ይፈልጋል፣

የማይችሉትን፣ ወጥተውም በልመና ለሚተዳደሩት ሕይወታቸውን ለማቅናት እንዲሁም ከችግር እንዲላቀቁ ማኅበሩ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ያስረዳሉ። ዕድሜያቸው ለገፋና እና መሰልጠን ለማይችሉ አቅመ ደካማ ዓይነ ሥውራን ሴቶች ደግሞ የምግብ፣ የንጽህና መጠበቂ፣ የአልባሳት እና የገንዘብ ድጋፎችን ያደርጋል።

ማኅበሩ በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ሴት ዓይነ ሥውራን እንዲሁም ያለ አባት ልጆቻቸውን ለሚያሳድጉ ዓይነ ሥውራን እናቶች የዳንቴል፣ የኮምፒውተር፣ የብሬል እና መሰል ሥልጠናዎች እንደሚሰጥ የተናገሩት የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ፤ እነኚህ ሴቶች በብዛት የሚተዳደሩት በልመና እና ሎተሪ በመሸጥ መሆኑን ገልፀዋል። ማኅበሩ ይህን ችግር በመረዳት ከልመና ወጥተው የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ጥረት እያደረገ ይገኛል። የእጅ ሥራ ሥልጠና ለወሰዱ ሴቶች ደግሞ የሠሩትን ዳንቴል ራሳቸውም ሆኑ ማኅበሩ በሚሳተፍባቸው የተለያዩ ባዛሮች ላይ በመገኘት ምርቶቻቸው እንዲሸጥ በማድረግ ገንዘብ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ሕይወታቸውን ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ ወይዘሮ ዘነበች ያስረዳሉ።

በሁለተኛ ደረጃ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ ችግረኛ ሴት ዓይነ ሥውራን ተማሪዎች በአቅም ማጣት ከትምህርት ገበታቸው እንዳይርቁ ለማድረግ የትራንስፖርት የሚሆን ገንዘብ ድጋፍ እያደረገ መሆኑንም አክለው ተናግረዋል።

ማኅበሩ ከተመሠረተ 11 ዓመታትን አስቆጥሯል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ሴት ዓይነ ሥውራን ቤታቸው ከሚቀመጡ እና የሰው እጅ ከሚያዩ እየሠሩ ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ ዕድሉን አመቻችቶላቸዋል። ከተለያዩ ዓይነ ሥውራን ጋር ስለሚገናኙም የተለያዩ እውቀቶችን እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር ማኅበራዊ ግንኙነታቸው እንዲጠናከር በር ከፍቷል። ማኅበሩ በእስካሁኑ ጉዞው ከ90 በላይ ሴት ዓይነ ሥውራንን በገንዘብ፣ የተለያዩ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግ ፣የበትር ድጋፍ፣ በምግብ እና በመሳሰሉት ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። በተጨማሪም ከማኅበሩ 120 አባላት ባሻገር ብዙዎችን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።

ይሁን እንጂ ማኅበሩ በችግር ላይ ነው። ከካናዳ በመሥራቿ በኩል ከሚገኝ የአልባሳት፣ የገንዘብ፣ የክር፣ የነጭ በትር (ኬን) ከሚያገኘው ድጋፍ ውጪ ሌላ ድጋፍ ባለማግኘቱ ብዙ መሥራት እንዳልተቻለና እንዲያውም አደጋ ላይ እንደሆነ ሥራ አስኪያጇ ይገልፃሉ። ሌላው ችግር የእጅ ሥራ ሥልጠና ለመስጠት አመቺ እና በቂ ቦታ ባለመኖሩ ማኅበሩ ከአቅም በላይ በሆነ መንገድ እየሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ማኅበሩ ከግለሰብ ቤት ተከራይቶ ድጋፍ እያደረገ ሲሆን፤ ድጋፍ የሚደርግለት አካል ቢያገኝ እንዲሁም የእጅ ሥራ ውጤቶቻቸውን ገዢ እንዲገኙ የገበያ ትስስር ቢፈጠር ከተቋቋመበት ዓላማ በተጨማሪ ብዙ ሥራ መሥራት እንደሚቻል ሥራ አስኪያጇ ይናገራሉ።

ዓይነ ሥውራን ሴት ተማሪዎች የሚማሩት ከዓይናማ ተማሪዎች (የዕይታ ችግር ከሌለባቸው) ጋር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም የኮምፒውተር ፣ ላፕቶፕ ፣ታብሌት እና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሶች እጥረት ስላለባቸው በርካቶች በትምህርታቸው እንደሚወድቁ የጠቆሙት ወይዘሮ ዘነበች ፤ በቀጣይ እንደዚህ ያሉትን ተማሪዎችን ለመደገፍ ታስቧል። ይሁን እንጂ ድጋፍ ለማግኘት አዳጋች ሆኗል ይላሉ።

በመንግሥት በኩል ያለው ድጋፍ አጥጋቢ እንዳልሆነ የገለጹት ሥራ አስኪያጇ፤ ከዚህ ቀደም በመንግሥት በኩል ስልጠና ይሰጥ እንደነበር ያስታውሳሉ። አሁን ግን የመቀዛቀዝ ነገር ይታያልና መንግሥትም ሆነ ሌሎች ደጋፊዎች የማኅበሩን ችግር ተመልክተው ድጋፍ ቢያደርጉ የብዙ ሴት ዓይነ ሥውራንን ሕይወት ለመቀየር እንደሚቻል ያስረዳሉ።

# ዓለም አቀፍ





ከኮቪድ 19 በፊት የቻይና አየር መንገዶች ወደ አሜሪካ የሚያደርጉት ሳምንታዊ በረራ 150 ነበር

## የቻይና አየር መንገዶች ወደ አሜሪካ የሚያደርጉትን ሳምንታዊ በረራ ወደ 50 እንዲያሳድጉ ተፈቀደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቻይና አየር መንገዶች ወደ አሜሪካ የሚያደርጉትን ሳምንታዊ በረራ ወደ 50 እንዲያሳድጉ ፈቃድ እንደሚሰጣቸው የአሜሪካ የትራንስፖርት ቢሮ አስታውቋል።

ለቻይና አየር መንገዶች የተፈቀደው ሳምንታዊ የበረራ ቁጥር ከኮቪድ 19 በፊት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር አንድ ሦስተኛው መሆኑንም ሮይተርስ ዘግቧል።

አሁን ላይ የቻይና አየር መንገዶች ወደ አሜሪካ የሚያደርጉት ሳምንታዊ በረራ 35 ሲሆን፣ ከፈረንጆቹ መጋቢት ወር መጨረሻ ጀምሮ ወደ 50 ያድጋል ተብሏል።

በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ የንግድ አውሮፕላን በረራ ቁጥር መጨመሩ አሜሪካ እና ቻይና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ወደ መደበኛ የመመለስ ሂደት ውስጥ ወሳኝ እርምጃ መሆኑን የአሜሪካ ትራንስፖርት ቢሮ አስታውቋል።

በፈረንጆቹ 2020 የኮቪድ 19 የጉዞ ክልከላ ከመጣሉ በፊት የአሜሪካ እና የቻይና አውሮፕላኖች በሳምንት ከ150 በላይ የደርሶ መልስ በረራዎችን ያደርጉ ነበር።

ሆኖም ግን ኮቪድ 19 ወረርሽኝን ተከትሎ እስከ ነሐሴ 2023 ድረስ የቻይና እና የአሜሪካ አየር መንገዶች የሚያደርጉት ሳምንታዊ በረራ በሳምንት ከ12 አይበልጥም ነበር ተብሏል።

## እሥራኤልና ሃማስ በረመዳን ፆም መግቢያ ተኩስ ያቆማሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ባይደን ተናገሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እሥራኤልና ሃማስ ከቀጣዩ ሳምንት ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ይደርሳሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ተናገሩ።

የእሥራኤልና ሃማስ አመራሮች ከኳታር እና አሜሪካ አደራዳሪዎች ጋር በተናጠል ግን በተመሳሳይ ከተማ (ዶሃ) እያካሄዱት ያለው ንግግር ተስፋ ሰጪ ነው ተብሏል።

እሥራኤል እስከ ረመዳን ፆም መግቢያ የተኩስ አቁም ስምምነት ካልተደረሰ በራፋህ ጦርነት እጀምራለሁ ማለቷም ድርድሩ እንዲፈጥን ማድረጉ ተገምቷል።

«የብሔራዊ ደህንነት አማካሪዬ ስምምነት ላይ ለመድረስ መቃረባችንን ነግሮኛል፤ ያላለቁ ጉዳዮች ቢኖሩም እስከ ቀጣዩ ሰኞ የተኩስ አቁም ስምምነት እንደሚደረስ ተስፋ አደርጋለሁ» ብለዋል ፕሬዚዳንት ባይደን።

የአሜሪካ አደራዳሪዎች እስከ መጋቢት 10 ድረስ አዲስ የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርሶ የታጋች እና እስረኞች ልውውጥ እንዲጀመር ግፊት እያደረጉ ነው።

እሥራኤልና ሃማስ ግን ለተኩስ አቁም ድርድሩ መጓተት እርስ በርስ መካሰስና የጋዛው ጦርነት መቀጠሉ አይቀሬ መሆኑን የሚያሳዩ ንግግሮችን ማድረጋቸውን ቀጥለዋል።

የሃማሱ የፖለቲካ ቢሮ ኃላፊ ኢስማኤል ሀኒየህ ከኳታሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ሼክ ታሚም ቢን ሀማድ አልታኒ ጋር ከመከሩ በኋላ በሰጡት መግለጫ፣ እሥራኤል የተኩስ አቁም ስምምነት እንዳይደረስ በማድረግ ፍልስጤማውያንን መግደሏን ቀጥላለች ብለዋል።

«የተኩስ አቁም ድርድሩን የወንጀሏ መደበቂያ እንድታደርገው አንፈቅድም» ማለታቸውንም ሬውተርስ ዘግቧል።

የእሥራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ በበኩላቸው ሀገራቸው የተኩስ አቁም ስምምነት ለመድረስ ዝግጁ ብትሆንም ሃማስ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች



እሥራኤልና ሃማስ በተናጠል ከኳታር አደራዳሪዎች ጋር በዶሃ እያደረጉት ያለው ምክክር ተስፋ ሰጪ ነው ተብሏል

ለድርድር የማይመጥኑ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ኔታንያሁ ከፎክስ ኒውስ ጋር ባደረጉት ቆይታ «አዲስ የተኩስ አቁም ስምምነት ለመድረስ ሃማስ ወደ እውነታው መምጣትና መወሰን አለበት» ሲሉ ተደምጠዋል።

በጋዛ የሚደረስ የትኛው የተኩስ አቁም ስምምነት በራፋህ የሚደረገውን ውጊያ አያስቆምም ማለታቸውም ተገልጿል።

ባለፈው ሳምንት በፓሪስ አሁን ደግሞ በዶሃ እየተደረገ በሚገኘው ድርድር የታጋቾች እና እስረኞች ልውውጥ እንዲሁም የሰብአዊ ድጋፍ ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ ሆነዋል።

እሥራኤል ከጋዛ ሙሉ በሙሉ እንድትወጣ ሃማስ ባቀረበው ቅድመ ሁኔታ ዙሪያ አደራዳሪዎቹ ያሉት ነገር ባይኖርም ቴል አቪቭ የተለወጠ አቋም እንደሌላት አስታውቃለች።

በራፋህ መሸጓል ያለችውን ሃማስ ለመደምሰስ የያዘችው እቅድ ንፁሃን እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ተፈፃሚ እንደሚሆንም ነው የገለፀችው።

በኳታር ከረመዳን ፆም መግቢያ ጀምሮ የሚተገበር የተኩስ አቁም ስምምነት ቢደረስም የፍልስጤማውያን ሰቆቃ በአጭር ጊዜ የሚቆም አይመስልም።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ሐሙስ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያውያን ኮከቦች በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ለድል ይጠበቃሉ

**ብርሃን ፈይሳ**



በቤት ውስጥ የዓለም ቻምፒዮና ኢትዮጵያን የሚወክለው ብሔራዊ ቡድን ከትናንት በስቲያ ወደ ግላስጎ አቅንቷል፤

19ኛው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በስኮትላንድ ግላስኮ ከነገ ጀምሮ ለሦስት ቀናት ይካሄዳል፡፡ የአጭርና መካከለኛ ርቀት ሩጫ እና የሜዳ ተግባራት ፉክክሮች በሚስተናገዱበት ቻምፒዮና በርካታ የኦሊምፒክ፣ የዓለም ቻምፒዮና እንዲሁም የውድድሩ የቀድሞ ባለድሎች ይሳተፉበታል፡፡ በዚህ ቻምፒዮና ከሚካፈሉት 133 ሀገሮች መካከል በተፎካካሪነታቸውና በርካታ የወርቅ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ቀዳሚ የሆኑት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ዘንድሮም ትልቅ የአሸናፊነት ግምት አግኝተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በቻምፒዮናው በጥቂት ፉክክሮች ብቻ ተካፍላ በውጤታማነት ከምታጠናቅቅባቸው መድረኮች አንዱ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ነው፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት በሰርቢያ ቤልግሬድ አስተናጋጅነት በተካሄደው 18ኛው ቻምፒዮና ኢትዮጵያ 4 የወርቅ፣ 3 የብር እና 2 የነሐስ በጥቅሉ 9 ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ አሜሪካና ቤልጂየምን አስከትላ ከዓለም አንደኛ ሆና ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ነገ በሚጀምረው የዘንድሮው ቻምፒዮና ላይም ይህንኑ ድል በማስቀጠል በርካታ ሜዳሊያ ይሰበስባሉ ተብለው ይጠበቃሉ፡፡ ከቀናት በፊት በተጠናቀቀው የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ላይ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አስደናቂ ውጤት ሲያስመዘግቡ የቆዩ ሲሆን፤ ከሳምንት በላይ በዘለቀው የብሔራዊ ቡድን ዝግጅትም አሸናፊነታቸው እንደሚቀጥል ተስፋ ተደርጓል፡፡

በውድድሩ ላይ ከሚካፈሉት 651 አትሌቶች መካከል 331 የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ፣ 320ው ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 18ቱ በቤልግሬዱ ውድድር ላይ ቻምፒዮን የነበሩ ስመጥር አትሌቶች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን ወክለው በውድድሩ ላይ ከሚካፈሉ አትሌቶች መካከልም በሁለቱም ጾታ በ1ሺ500 እና 3ሺ ሜትር ቻምፒዮናዎች (ሳሙኤል ተፈራ፣ ጉዳፍ ጸጋይ፣ ሰለሞን ባረጋ፣ ለምለም ኃይሉ) በድጋሚ ግላስኮ ላይ ለድል ይሮጣሉ፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በቻምፒዮናው በ5 ወንድ እና 8 ሴት አትሌቶች ስትወከል፤ 800 ሜትር፣ 1ሺ500 ሜትር እና 3ሺ ሜትር ርቀቶች ጠንካራ ፉክክር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በሴቶች 800 ሜትር ሃብታም ዓለሙ እና ጽጌ ድጉማ ኢትዮጵያን ወክለው የሚሮጡ ሲሆን፤ ለሜዳሊያ ከሚፎካከሩ አትሌቶች መካከል ይገኙበታል፡፡ በተለይም በዚህ ርቀት ከፍተኛ ልምድ ያካበተችው አትሌት ሃብታም አለሙ ለወርቅ ሜዳሊያ የቀረበ ቅድመ ግምት አግኝታለች፡፡ አትሌቷ በሦስት የቤት ውስጥ ቻምፒዮና የተሳትፎ ታሪክ ያላት ሲሆን፤ እ.አ.አ 2016 ተሳትፎዋ ስድስተኛ ደረጃን ይዛ ስታጠናቅቅ፣ እ.አ.አ በ2018 ሁለተኛ እንዲሁም በ2022 ሰባተኛ ሆና ፈጽማለች፡፡ በቅርቡ በተካሄደው የወርቅ ደረጃ ያለው የሌቪን የቤት ውስጥ የዙር ውድድር አሸናፊ የነበረችው ሃብታም 1:57.86 የሆነ የግሏን ሰዓት አስመዝግባ ነበር። ይኸውም በጥሩ አቋም ላይ የምትገኝና ለአሸናፊነት የሚያበቃት መሆኑን ያመላክታል፡፡ በዚህ ርቀት በወንዶች በኩል አትሌት ኤፍሬም መኮንን በብቸኝነት ኢትዮጵያን ይወክላል፡፡

በሁለቱም ጾታ ኢትዮጵያ በርካታ ሜዳሊያ ትሰበስባለች ተብሎ ከሚጠበቁ ርቀቶች መካከል አንዱ የ1ሺ500 ሜትር ውድድር ነው፡፡ ቤልግሬድ ላይ ኢትዮጵያ ቻምፒዮን መሆኗን ተከትሎ ሦስት አትሌቶችን የማሳተፍ ዕድል ባገኘችበት የሴቶች ውድድር፤ አትሌት ፍሬወይኒ ኃይሉ፣ ድርቤ ወልተጂ እና ብርቄ ኃየሎም ይፎካከራሉ፡፡ እጅግ ጠንካራ የተባለው ይህ ቡድንም እንደተለመደው ሜዳሊያዎቹን ጠራርጎ እንደሚወስድ የተገመተ ሲሆን፤ ቤልግሬድ ላይ በ800 ሜትር የብር ሜዳሊያ ባለቤት የነበረችው ፍሬወይኒ ጉዳፍን ተከታ ድል እንደምታስመዘግብ ትጠበቃለች፡፡ አትሌቷ የተያዘውን የውድድር ዓመት የወርቅ ደረጃ ባላቸው የአስትራቫ እና ሌቪን የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች በአንድ ማይል እና 1ሺ500 ሜትር አሸናፊ ነበረች፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት በ3ሺ ሜትር የነሐስ ባለቤት የነበረችው እጅጋየሁ ታዬም ዘንድሮ ርቀቷን ቀይራ ከሀገሯ ልጆች ጋር ሜዳሊያ ለማጥለቅ ትሮጣለች፡፡

ጠንካራ ፉክክር እንደሚያስተናግድ በሚጠበቀው የወንዶች 1ሺ500 ሜትር ርቀትም ቻምፒዮኑ ሳሙኤል ተፈራ ኢትዮጵያን በድጋሚ ባለድል ለማድረግ ይፋለማል፡፡ እ.አ.አ በ2018 በርሚንግሃም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በቻምፒዮናው የተሳተፈው የ24 ዓመቱ አትሌት አሸናፊ መሆኑን ተከትሎ በ2022 ቻምፒዮና በቀጥታ የመሳተፍ ዕድል ሲያስገኝለት በድጋሚ የወርቅ ሜዳሊያውን ማጥለቅም ችሏል፡፡ ግላስኮ ላይም ለሦስተኛ ጊዜ የኢትዮጵያን ባንዲራ ለማውለብለብ ከወጣቱ አትሌት ቢኒያም መሃሪ ጋር የሚሰለፍ ይሆናል፡፡

በአትሌቲክስ ቤተሰቡ ዘንድ እጅግ በጉጉት የሚጠበቀው የ3ሺ ሜትር ርቀትም በሁለቱም ጾታ በኢትዮጵያውያን አትሌቶች አሸናፊነት ይጠናቀቃል የሚለው ሚዛን የሚደፋ ሆኗል፡፡ በቤልግሬድ የ1ሺ500 ሜትር ቻምፒዮን የነበረችው ጠንካራዋ አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ቡድኑን የምትመራ ሲሆን፤ ፉክክሯ ከሀገሯ ልጅ በ2022 የ3ሺ ሜትር ቻምፒዮና ለምለም ኃይሉ ጋር ይሆናል።

በወንዶች የ3ሺ ሜትር ርቀት የኦሊምፒክና የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮኑ ሰለሞን ባረጋ የኢትዮጵያን ቡድን ይመራል፡፡ ቡድኑ በቤልግሬድ ቻምፒዮና መሆኑን ተከትሎ ሦስት አትሌቶችን የማሳተፍ ዕድል ቢያገኝም አትሌት ጥላሁን ኃይሌ ከቡድኑ ጋር አለመጓዙ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በርቀቱ ውጤታማ የሆነው ሰለሞን ከሌላኛው ጠንካራ አትሌት ጌትነት ዋለ ጋር ለአሸናፊነት ይፎካከራሉ፡፡

SACUUR REAL ESTATE

የሽያጭ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ሳኩር ሪልስቴት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በመሃል ካዛንቺስ ራዲሰን ብሉ ሆቴል ጀርባ ሙሉ በሙሉ ገንብቶ ያጠናቀቀው እና ከአንድ አመት በፊት ለቤት ባለቤቶች ያስረከበው ዘመናዊ አፓርትመንት ህንጻ 15+ኛ ወለል ላይ የሚገኙ ፔንት ሃውሶች እና የመጀመሪያ ወለል ላይ የሚገኘውን የንግድ ስፍራ ለሽያጭ አቅርቧል፡ ቤቶቹ የራሳቸው የተናጠል ካርታ ያላቸው ሲሆን ግንባታቸው 100% የተጠናቀቀ በመሆኑ ለማከራየትም ሆነ ለመኖር ዝግጁ ከመሆናቸውም በላይ በዘመናዊ የቤት እቃዎች ተሟልተው እርሶን ይጠብቃሉ፡፡

ስለንብረቶቹ ዝርዝር መረጃን ለማግኘት እና ለመጎብኘት በስልክ ቁጥሮቻችን +251920060606/0952060606 በመደወል መረጃዎቹን ማግኘት አልያም በአካል ለመጎብኘት ካዛንቺስ ኢሲኤ አጠገብ ራዲሰን ብሉ ሆቴል ጀርባ በመምጣት መጎብኘት የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን፡፡



ሳኩር ሪልስቴት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር
የአልሳም ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እህት ኩባንያ